# የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቶች ወደ ገላትያ፣ ኤፌሶን፣ ተሰሎንቄ ሰዎች እና ፊልሞና

EECD
የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በዴንቨር

“ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን”

በዴንቨር ኮሎራዶ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት ኅብረት የተዘጋጀ

June 2025
2nd Edition

ማውጫ


የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች ..... 1

***መግቢያ*** ..... ***1***

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 1*** ..... ***2***

***አንድ ወንጌል፤ ገላ. 1፥1-10*** ..... ***2***

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 2*** ..... ***3***

*የጳውሎስ የሐዋርያነት ጥሪ፤ ገላ. 1፥11-24* ..... 3

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 3*** ..... ***4***

*የጳውሎስ ሐዋርያነት ለሌሎች መታወቅ፤ ገላ. 2፥1-10* ..... 4

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 4*** ..... ***5***

*ጳውሎስ ጴጥሮስን ማረሙ፤ ገላ. 2፥11-21* ..... 5

***ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 5*** ..... ***6***

*የገላትያ ሰዎች አለማስተዋል፤ ገላ. 3፡1-5* ..... 6

***ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 6*** ..... ***7***

*ጽድቅ በእምነት ወይስ ሕግን በመጠበቅ? ገላ. 3፡6-14* ..... 7

***ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 7*** ..... ***8***

*ሕግ እና የተስፋው ቃል፤ ገላ. 3፡15-22* ..... 8

***ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 8*** ..... ***9***

*የእግዚአብሔር ልጅነት (ክፍል 1)፤ ገላ. 3፡23-29* ..... 9

***ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 9*** ..... ***10***

*የእግዚአብሔር ልጅነት (ክፍል ሁለት)፤ ገላ. 4፡1-7* ..... 10

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 10*** ..... ***11***

*ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የነበረው ናፍቆት፤ ገላ. 4፡8-20* ..... 11

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 11*** ..... ***12***

*የአጋር እና የሣራ ምሳሌነት፤ ገላ. 4፡ 21-31* ..... 12

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 12*** ..... ***13***

*በነጻነት ጸንቶ መኖር (ክፍል አንድ)፤ ገላ. 5፡1-7* ..... 13

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 13*** ..... ***14***

በነጻነት ጸንቶ መኖር (ክፍል ሁለት)፤ ገላ. 5፡8-15 ..... 14

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 14*** ..... ***15***

*የሥጋና የመንፈስ መቀዋወም፤ ገላ. 5፡16-26* ..... 15

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 15*** ..... ***16***

*የደከመውን ማቅናት፤ ገላ. 6፡1-6* ..... 16

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 16*** ..... ***17***

*የዘሩትን ማጨድ፤ ገላ. 6፡7-10* ..... 17

***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 17*** ***18***
*ሌላ ትምክህትን ማራቅ፤ ገላ. 6፥11-18* 18
የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች 19
***መግቢያ*** ***19***
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 1*** ***20***
*በክርስቶስ ያገኘነው በረከት፤ ኤፌ. 1÷1-8* 20
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 2*** ***21***
*ሁሉ በክርስቶስ መጠቅለሉና በመንፈስ ቅዱስ መታተማችን፤ ኤፌ. 1÷9-14* 21
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 3*** ***22***
*የምስጋናና የልመና ጸሎት፤ ኤፌ. 1÷15-23* 22
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 4*** ***23***
*በክርስቶስ ሕያው መሆን፤ ኤፌ. 2÷1-10* 23
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 5*** ***24***
*በክርስቶስ አንድ መሆን፤ ኤፌ. 2÷11-22* 24
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 6*** ***25***
*የጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያነት፤ ኤፌ. 3÷1-13* 25
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 7*** ***26***
*ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው ጸሎት፤ ኤፌ. 3÷14-21* 26
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 8*** ***27***
*መንፈሳዊ አንድነት፤ ኤፌ. 4÷1-6* 27
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 9*** ***28***
*ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ የጸጋ ስጦታዎችና ዐላማቸው፤ ኤፌ. 4÷7-16* 28
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 10*** ***29***
*ከንቱ አዕምሮና የታደሰ አዕምሮ፤ ኤፌ. 4÷17-24* 29
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 11*** ***30***
*ቅዱሱን መንፈስ አታሳዝኑ፤ ኤፌ. 4÷25-32* 30
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 12*** ***31***
*እንደ ተወደዱ ልጆች መመላለስ፤ ኤፌ. 5÷1-7* 31
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 13*** ***32***
*ዘመኑን ዋጁ፤ ኤፌ. 5÷8-20* 32
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 14*** ***33***
*አማኝ ባለ ትዳሮች፤ ኤፌ. 5÷21-33* 33
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 15*** ***34***
*ክርስቲያናዊ ቤተ ሰብ፣ ሠራተኞችና አሰሪዎች፤ ኤፌ. 6÷1-9* 34
***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 16*** ***35***
*መንፈሳዊ ውጊያ፤ ኤፌ. 6÷10-24* 35
መጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 36

***መግቢያ*** ... ***36***
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 1*** ... ***37***
*እግዚአብሔርን የሚያስመሰግን ሕይወት፤ 1ኛ ተሰ. 1÷1-4* ... 37
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 2*** ... ***38***
*በምሳሌነት መመላለስ፤ 1ኛ ተሰ. 1÷5-10* ... 38
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 3*** ... ***39***
*የሐዋርያው ጳውሎስ የወንጌል ተጋድሎ፤ 1ኛ ተሰ. 2÷1-12* ... 39
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 4*** ... ***40***
*ቃሉን እንደ እግዚአብሔር ቃል መቀበል፤ 1ኛ ተሰ. 2÷13-20* ... 40
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 5*** ... ***41***
*በመከራ መጽናት፤ 1ኛ ተሰ. 3÷1-5* ... 41
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 6*** ... ***42***
*በመጽናት መጽናናት፤ 1ኛ ተሰ. 3÷6-13* ... 42
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 7*** ... ***43***
*በቅድስና መመላለስ፤ 1ኛ ተሰ. 4÷1-8* ... 43
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 8*** ... ***44***
*የእርስ በርስ ፍቅርና የሥራ ትጋት፤ 1ኛ ተሰ. 4÷9-12* ... 44
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 9*** ... ***45***
*ተስፋ እንደ ሌላቸው እንዳታዝኑ፤ 1ኛ ተሰ. 4÷13-18* ... 45
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 10*** ... ***46***
*እንግዲያስ እንንቃ፤ 1ኛ ተሰ. 5÷1-11* ... 46
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 11*** ... ***47***
*ለመሪዎችና ለሕዝቡ የተሰጠ ኀላፊነት፤ 1ኛ ተሰ. 5÷12-18* ... 47
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 12*** ... ***48***
*የመደምደሚያ ምክሮች፤ 1ኛ ተሰ. 5÷19-28* ... 48
ሁለተኛይቱ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ስዎች ... 49
***መግቢያ*** ... ***49***
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 1*** ... ***50***
*የምስጋናና የልመና ጸሎት፤ 2ተኛ ተሰ. 1÷1-12* ... 50
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 2*** ... ***51***
*ማንም አያስታችሁ፤ 2ኛ ተሰ. 2÷1-12* ... 51
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 3*** ... ***52***
*ጸንታችሁ ቁሙ፤ 2ኛ ተሰ. 2÷13-18 ፤ 3፥1-5* ... 52
***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 4*** ... ***53***
*መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ፤ 2ኛ ተሰ. 3÷6-18* ... 53
የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና ... 54
***መግቢያ*** ... ***54***

***ወደ ፊልሞና ጥናት 1*** ***55***
*ሰላምታ፣ ምስጋና እና ጸሎት፤ ፊልሞና 1-7* 55
***ወደ ፊልሞና ጥናት 2*** ***56***
ጳውሎስ ስለ አናሲሞስ ለፊልሞና ያቀረበው ጥያቄ (ክፍል አንድ)፤ ፊልሞና 8-16 56
***ወደ ፊልሞና ጥናት 3*** ***57***
*ጳውሎስና ስለ አናሲሞስ ለፊልሞና ያቀረበው ጥያቄ (ክፍል ሁለት)፤ ፊልሞና 17-25* 57

**የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች**

**መግቢያ**
በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ ሃያ አንድ ደብዳቤዎች መካከል ዐሥራ ሦስቱ በሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ተጻፉ ይታመናል። የገላትያ መልእክት ከእነዚህ ከዐሥራ ሦስቱ ደብዳቤዎች መካከል በቀዳሚነት ከተጻፉት ውስጥ አንዱ መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ። ሌላው ይህ ደብዳቤ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ተዘዋውረው እንዲነበቡ ከተላኩ መልእክቶች (circular letters) መካከል አንዱ መሆኑንም መጥቀስ ይቻላል። ዐውዱን በጠበቀ መልኩ የዚህን ደብዳቤ ይዘት ጠጋ ብለን ለማንበብና ለመወያየት ይረዳን ዘንድ የመልእክቱን ታሪካዊ ዳራ በአጭሩ በመዳሰስ እንጀምራለን።

**ጸሐፊ**፤ የገላትያ መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መሆኑ በመክፈቻ ቁጥር ላይ በግልጽ ተጽፏል፤ “በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታንም ባነሣው በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ እንጂ ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ ጳውሎስ ከእኔም ጋር ያሉት ወንድሞች ሁሉ …” (ቁጥር 1) ይላል። የሐዋርያው ጳውሎስን ጸሐፊነት በተመለከተ እንደ ተጨማሪ ማስረጃ የሚከተሉትን ክፍለ ምንባባት መመልከት ይቻላል (1÷20፤ 5÷2፤ 6÷11)።

**ተቀባይ**፤ “ወደ ገላትያ አብያተ ክርስቲያናት” (ቁጥር 1) የሚለው ሐረግ እንደሚያመለክተው መልእክቱ የተጻፈው በገላትያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ማለትም በሮም አገዛዝ ዘመነ መንግሥት በትንሿ እስያ በአሁኗ ቱርክ ገላትያ አውራጃ ውስጥ ለነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ነበር። በገላትያ ሰሜናዊ ክፍል ወይስ ደቡባዊ ክፍል የሚለው ጥያቄ አከራካሪና የሐሳብ ልዩነቶች የሚንጸባረቁበት ቢሆንም በገላትያ ደቡባዊ ክፍል ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መሆኑ በብዙዎች ዘንድ ይታመናል። እነዚህም የደቡብ ገላትያ አውራጃ ከተሞች ማለትም ጲስድያ፣ አንጾኪያ፣ ኢቆንዮን፣ ልስጥራን እና ደርቤ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ የተመሠረቱትም ሐዋርያው ጳውሎስ ከበርናባስ ጋር ባደረገው በመጀመሪያ የወንጌል ጉዞው ወቅት ነበር። የበለጠ ለመረዳት የሐዋርያት ሥራ ምእራፍ 13 እና 14 ን ያንብቡ።

**የተጻፈበት ጊዜና ቦታ**፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የገላትያን መልእክት ከአንጾኪያ ምናልባትም በ48 ዓ.ም ወይም በ49 ዓ.ም አካባቢ እንደ ጻፈ ይታመናል። ከመልእክቱ ይዘት በመነሳት ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በሐዋርያት ሥራ 15 ላይ ከተካሄደው ከኢየሩሳሌም ጉባዔ በፊት እንደ ሆነም መናገር ይቻላል።

**የመልእክቱ ዐላማ**፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መልእክት እንዲጽፍ በጊዜው ያስገደደው ዋናው ምክንያት በገላትያ የሚኖሩ አይሁድ ያልሆኑ አማኞች ከአይሁድ ዘር በሆኑ ክርስቲያኖች ግፊት ወደ ተሳሳተ ትምህርት እየገቡ መሆኑ ነበር። የስህተት ትምህርቱ አሕዛብ ድነት ለማግኘት በክርስቶስ ከማመን በተጨማሪ የሙሴን ሕግ እና ሌሎችንም የአይሁድን ትእዛዛት መጠበቅ አለባቸው የሚል ትኩረት ነበረ። በመሆኑም መልእክቱ የተጻፈበት ዋና ዐላማ በክርስቶስ የተገኘውን አርነት ለማሳየትና ከአይሁድ ወገን በመጡ ክርስቲያኖች የተፈጠሩትን የተሳሳተ አመለካከት ለማስተካከል ነው።

ይህንን ትምህርት ለመመከት ሐዋርያው ጳውሎስ በአራት ዋና ዋና ሐሳቦች ላይ ሲያተኩር እናያለን። እነዚህ አራቱ ሐሳቦች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡- አንደኛ፤ ሰው ሕግና ትእዛዛትን በመጠበቅ ለድነት እንደማይበቃና ለመዳን ብቸኛው መንገድ ሰው ሁሉ ኀጢአተኛነቱን አምኖ በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ማመን እንደሚጠበቅበት ለማስገንዘብ፤ ሁለተኛ፤ ከእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ ለመዳን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀው መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነ ለማጽናት፤ ሦስተኛ፤ እግዚአብሔር የሰው ልጆች ሁሉ ከኀጢያት ባርነት ነጻነት እንዲወጡ የዘጋጀው መንገድ ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ እንደ ሆነና ከዚህ እውነት በመራቅ ራሳቸውን የሕግ እና የልዩ ልዩ ትእዛዛት ባሪያ እንዳያደርጉ ለመምከር እና አራተኛ፤ የገላትያ አማኞች የዳኑት መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥ በገለጸው ጸጋ ብቻ እንደ ሆነና ይህም መንፈስ ሕይወታቸውን እንደሚመራ፣ እንደሚጠብቅና መንገዱንም እንዲሚያሳያቸው ለማመልከት ነው።

## *ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 1*

## *አንድ ወንጌል፤ ገላ. 1÷1-10*

### *መግቢያ*

በዚህ በመጀመሪያው ጥናት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን በሰላምታ ከጀመረ በኋላ በገላትያ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በፍጥነት ወደ ሌላ ወንጌል ዘወር እንዳሉ በማሳየት እንዴት እንደ ሞገታቸው እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 1-2 ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን *"በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ እንጂ ከሰው ያልሆነ"* ብሎ ያስተዋወቀው ለምን ይመስላችኋል?
2. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኀጢአታችን ራሱን የሰጠው ለምንድን ነው? (ቁጥር 4)
3. በቁጥር 6 ላይ ጳውሎስ፤ *"ልዩ ወንጌል"* ብሎ የጠቀሰው ምን እንደ ሆነ አብራሩ።
4. ከቁጥር 7 እስከ 9 ስናነብ ጳውሎስ *"የተረገመ ይሁን"* የሚለውን ቃል የተጠቀመው ለእነማን ነው?
5. በቁጥር 10 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ *"አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ብልሆንሁም"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።

### *ከሕይወት ጋር ማዛመድ*

- ዛሬም በዚህ ዘመን የምናያቸው አንዳንድ በቃሉ ላይ ያልተመሠረቱ ልዩ ትምህርቶች እና ልምምዶች አሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ካሉ የተወሰኑትን በመጥቀስ በምን መልኩ በእውነት ጸንተን በመቆም ራሳችንና ሌሎችን መጠበቅ እንደምንችል እናስብ፤ እንመካከርም። ለመሆኑ እነዚህን ልዩ ትምህርቶችና ልምምዶች በመመከት ለእውነት ለመቆም ምን ያህል ተዘጋጅተናል?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### *ማጠቃለያ*

ሐዋርያው ጳውሎስ በዛሬው ክፍለ ምንባብ ድነት የሚገኘው ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ሞት የከፈለውን ዋጋ አምኖ በመቀበል ብቻ መሆኑን እና ከዚህ የተለየ አዲስ የመጣ የስህተት ትምህርት ነፋስ ሁሉ ሊያናውጠንና በክርስቶስ ያገኘነውን ነጻነት መልሶ ሊነጥቀን የመጣ እንደ ሆነ ያሳየናል። ሕግና ትእዛዛትን መጠበቅ መልካም ቢሆንም ለመዳን ግን የሚያስፈልገን በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ብቻ እንደ ሆነ በሚገባ መረዳት ይገባናል።

### *በቃል የሚጠና ጥቅስ*

*"አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።"* (ገላ. 1÷9)

## ***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 2***

## ***የጳውሎስ የሐዋርያነት ጥሪ፤ ገላ. 1÷11-24***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ የነበሩ አማኞች በፍጥነት ወደ ሌላ ወንጌል ዘወር ስላሉ እንዴት እንደ ወቀሰቻው በመመልከት ጥሩ ውይይት ማድረጋችን ይታወሳል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጳውሎስ ለሐዋርያነት እንዴት እንደ ተጠራ እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ከቁጥር 11-12 የጳውሎስን የሐዋርያነት ጥሪና የሚሰብከውን ወንጌል ከማን እንደ ተቀበለው አብራሩ።
2. ከቁጥር 13-14 የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ያለ ልክ እንዲያሳድድና እንዲያጠፋ ጳውሎስን ያነሳሳው ምክንያት ምን ነበር?
3. በቁጥር 15 እና 16 መሠረት ጳውሎስ በአይሁድ ሥርዐት መኖሩና ለአባቶችም ወግ ከመጠን ይልቅ ከመቅናቱ የተነሳ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ያለ ልክ ያሳድድና ያጠፋ ከነበረበት ሕይወት ወደ ክርስቶስ ሐዋርያነት ሊለወጥ የቻለው እንዴት ነው?
4. ከቁጥር 17-22 በማንበብ የተረዳችሁትን ሐሳብ ለሌሎች አካፍሉ።
5. በቁጥር 23 እና 24 የአይሁድ ማኅበር ስለ ጳውሎስ የነበራቸውን አሉታዊ አመለካከት አስወግደው ስለ እርሱ እግዚአብሔርን ያከበሩበት ምክንያት ምንድን ነው?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ሐዋርያው ጳውሎስ ለጥሪው ከሰጠው ምላሽ በመነሳት ዛሬ በዚህ ዘመን ጌታ ለሥራው ቢጠራህ/ሽ እሺ ብለህ/ሽ ለመታዘዝ ምን ያህል ዝግጁ ነህ/ሽ?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታ ለአገልግሎት ሲለየው ከሥጋ እና ከደም ጋር ሳይመካከር፣ ያደገበትን ሕግ እና ሥርዐት በመተው፣ ለጌታ ታዛዥ በመሆን፣ ራሱን ሰጥቶ ለጥሪው ታማኝ በመሆን ማገልገሉን በግልጽ ተረድተናል። ከሐዋርያው ምላሽ ትምህርት ቀስመን እኛም ለጌታ በመታዘዝ በተጠራንበት ልዩ ልዩ ጥሪ/አገልግሎት ራሳችንን ሰጥተን በታማኝነት ልናገለግል ይገባናል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም"* (ገላ. 1፥16)

## ***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 3***

## ***የጳውሎስ ሐዋርያነት ለሌሎች መታወቅ፤ ገላ. 2÷1-10***

### ***መግቢያ***

በጥናት ሁለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለአገልግሎት እንዴት እንደ ተጠራ አይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ከጌታ የተቀበለው የአገልግሎት ጥሪ በሌሎች አገልጋዮች ዘንድ እንዴት ተቀባይነት እንዳገኘ እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 1 እና 2 እንደ ተገለጸው ሐዋርያው ጳውሎስ ከዐሥራ አራት ዓመት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም መመለሱና ትምህርቱን ለሌሎች አገልጋዮች ማስታወቁ ለምን ነበር?
2. ከቁጥር 3 እስከ 5 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ *"በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነታችንን ... ለአንድ ሰዓት እንኳ ለቅቀን አልተገዛንላቸውም"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ አብራሩ።
3. በቁጥር 6 ሐዋርያው ጳውሎስ *"አለቆች የመሰሉት ግን በፊት ማን እንደ ነበሩ አይገደኝም"* ሲል ምን ለማለት ፈልጎ እንደ ሆነ ተወያዩ።
4. ቁጥር 7 እና 8 ን በማንበብ ጴጥሮስ "ለተገረዙት ሐዋርያ" ጳውሎስ ደግሞ "ለአሕዛብ ሐዋርያ" የመሆናቸውን ልዩነት አብራሩ።
5. በቁጥር 9 እና 10 መሠረት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለጳውሎስና ለበርናባስ ቀኝ እጃቸውን የመስጠታቸው ጥቅም ምን ይመስላችኋል?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ጌታ ለአገልግሎት ጠርቶኛል ብላችሁ ታምናላችሁ? ከሆነስ እንደ ጥሪያችሁ እያገለገላችሁ ስለ መሆኑ፣ ስለ አገልግሎታችሁ ከሌሎች ወገኖች በተለይም ከመሪዎች ምክር ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? እስከ ዛሬ ይህን አድርጋችሁ የማታውቁ ከሆነ ከእንግዲህስ ምን ለማድረግ ታስባላችሁ?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ሐዋርያው ጳውሎስ በተጠራበት የወንጌል አገልግሎት ጥሪ ለበርካታ ዓመታት ካገለገለ በኋላ የአስተምህሮውን ወጥነት ለማጽናት በኢየሩሳሌም ከነበሩ መሪዎች ጋር እንደ ተነጋገረ ተመልክተናል። ይህ የሚያሳየን እኛም በተጠራንበት ልዩ ልዩ የአገልግሎት ጥሪ ጌታን እያገለገልን ሳለ የአገልግሎታችንን ጤናማነት ለመፈተሽ ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን ወይም የአገልግሎት መሪዎቻችን ጋር በመሆን ራሳችንን ዝቅ አድርገን እንደ ቃሉ መመርመር እንደሚገባን ነው።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

"ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆን ለጴጥሮስ የሠራለት፥ ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቶአልና።"

(ገላ. 2÷8)

## ***<u>ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 4</u>***

## ***<u>ጳውሎስ ጴጥሮስን ማረሙ፤ ገላ. 2÷11-21</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ የተቀበለው የአገልግሎት ጥሪ በሌሎች አገልጋዮች ዘንድ እንዴት ተቀባይነት እንዳገኘ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋርያው ጴጥሮስን ለማረም ፊት ለፊት የተቃመወበትን ምክንያት በዝርዝር እናያለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. ከቁጥር 11 እስከ 14 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ፡ ሐዋርያው ጴጥሮስን የተቃወመበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።
2. በቁጥር 15 *"እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም"* የሚለውን ሐሳብ በሮሜ 3÷23 *"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል"* ካለው ጋር እንዴት ትረዱታላችሁ?
3. በኀጢአት ለወደቁ የሰው ልጆች ሁሉ (አይሁድም ሆኑ አሕዛብ) የጽድቅ ብቸኛው መንገድ በየት በኩል በመሄድ እና ምን በማድረግ እንደ ሆነ ገላትያ 2÷16-21 እና ሮሜ 3÷24-30 ን በማንበብ ተነጋገሩ።
4. በቁጥር 20 ሐዋርያው ጳውሎስ፡ *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል"* ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?
5. በቁጥር 21 *"የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፤ ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ"* የሚለውን ሐሳብ በማብራራት ተወያዩ።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- ዛሬም በዚህ ዘመን በግብዝነት የምናደርጋቸው አንዳንድ መንፈሳዊ የሚመስሉ ግን ያልሆኑ ልምምዶችን በመጥቀስ ከቡድን አባላት ጋር ተወያዩ።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ምንም እንኳ ሐዋርያው ጴጥሮስ የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ዋና መሪ ቢሆንም ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ሲያፈገፍግና እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄደ ሐዋርያው ጳውሎስ ባየው ጊዜ ይህን ስህተት ለማረም ሐዋርያው ጴጥሮስን ፊት ለፊት መቃወሙን ተመልክተናል። እኛም ባለንበት ዘመን ምንም ዐይነት ስምና የትኛውም ደረጃ የተሰጣቸው አገልጋዮች ቢሆኑ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሸቃቅጡ ከሆኑ በምንም ሳናመቻምች እውነትን በፍቅር ልንገልጥ ይገባናል። በክርስቶስ ከማመን በቀር ሌላ የጽድቅ አማራጭ መንገድ የለም።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል።"* (ገላ. 2÷16)

## *ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 5*

## *የገላትያ ሰዎች አለማስተዋል፤ ገላ. 3፥1-5*

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጴጥሮስ ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ሲያፈገፍግና እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄደ ሐዋርያው ጳውሎስ ባየው ጊዜ ይህን ስህተት ለማረም ፊት ለፊት እንደ ተቃወመው አይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ አለማስተዋላቸው ለገላትያ ሰዎች ያቀረበላቸውን ጥያቄዎች በዝርዝር እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው የገላትያ አማኞች የተወቀሱበት አለማስተዋል ምን ነበር? አዚም ማለትስ ምን ማለት ነው?
2. በቁጥር 2 ላይ *"በሕግ ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁን?"* ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የገላትያ ሰዎች መልሳቸው ምን ይመስላችኋል?
3. በቁጥር 3 በመንፈስ የጀመሩት የገላትያ ሰዎች ባለማስተዋል እንዴት በሥጋ ሊፈጽሙት እንደ ሆነ አብራሩ።
4. በቁጥር 4 ላይ *"በውኑ ከንቱ እንደ ሆነስ እንደዚህ ያለ መከራ በከንቱ ተቀበላችሁን?"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. ቁጥር 5 "እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተ ዘንድ ተአምራት የሚያደርግ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማት ነው?" ለሚለው ምላሹ ምንድን ነው? መልሳችሁ ይብራራ።

### *ከሕይወት ጋር ማዛመድ*

- እኛም እንደ ገላትያ ሰዎች ካላስተዋልን ለእውነት እንዳንታዘዝ ባለንበት ዘመን ምን ዐይነት አዚም ሊደረግብን ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### *ማጠቃለያ*

የክርስትናን ሕይወት የጀመርነው መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራልንን ሥራ እንድናይ መንፈሳዊ ዐይኖቻችንን ስላበራ ነው። በእምነት ጉዞ ላይ እስካለን ድረስ ከክርስቶስ ላይ ዐይናችንን እንድናነሳና ለእውነት እንዳንታዘዝ አዚም ሊያደርግብን የሚችል መንፈሳዊ ተግዳሮት ሊገጥመን ይችላል። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስን ሰምተን ክርስቶስን በእምነት ተቀብለን የጀመርነውን ሕይወት በመንፈስ ልንፈጽመው እንድንችል ዐይናችንን ከመስቀሉ ላይ ላለማንሳት በነገር ሁሉ በማስተዋል ልንጸና ይገባናል።

### *በቃል የሚጠና ጥቅስ*

*"የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?"* (ገላ. 3፥1)

## ***ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 6***

## ***ጽድቅ በእምነት ወይስ ሕግን በመጠበቅ? ገላ. 3፥6-14***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ለገላትያ ሰዎች አለማስተዋል ሐዋርያው ጳውሎስ ያቀረባቸውን መሠረታዊ ጥያቄዎች በዝርዝር ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጽድቅ የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ በሕግ አለመሆኑና ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን በመሆን ከሕግ ርግማን እንደ ዋጀን ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ አማኞች ያስረዳበትን እንዳስሳለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 6 ላይ *"እንዲሁ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነና ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት"* ይላል፤ *"ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት"* የሚለው ምን ማለት እንደ ሆነ አብራሩ።
2. በቁጥር 8 እና 9 ያለውን ሐሳብ ከዘፍጥረት 12፥3 ጋር በማስተያየት እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰበከው ወንጌል ምን የሚል እንደ ነበረ አብራሩ። ያ ተስፋስ የተፈጸመ ይመስላችኋል?
3. ከቁጥር 10 እስከ 12 በማንበብ *"በእርግማን በታች"* መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ እና *"ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።
4. በቁጥር 13 *"ክርስቶስ ለእኛ እርግማን ሆነ"* ማለት ምን ማለት ነው? *"ከሕግ እርግማን ዋጀን"* ማለትስ?
5. በቁጥር 14 መሠረት አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የተቀበልነው የመንፈስ ተስፋ ምንድን ነው?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- መባረክ ማለት ምን ማለት ነው? መርገም ማለትስ? ከአሕዛብ ወገን የሆንን ግን ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት አምነን በተዋጀን በእኛ ላይ የትኛውም ዐይነት መርገም ሊሠራብን የሚችል ይመስላችኋል?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

*"በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና"* ከሚለው የሕግ ርግማን ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ዋጀን። ይህ የሰማያዊ በረከት ተስፋ ደግሞ እግዚአብሔር ራሱ ለአብርሃም የሰበከው ወንገል ነው። እኛም ክርስቶስን አምነን ስለተቀበልን *"ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ"* በሚለው ቃል መሠረት ከተባረከው የአብርሃም ዘር ሆነናል። ስለዚህ ያጸደቀን ሕግ ሳይሆን በክርስቶስ ማመናችን ነው። በመሆኑም መርገም በእኛ ላይ አይሠራም። ከሕግ ርግማን ዋጅቶ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ለባረከን ጌታ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ይሁን። አሜን!

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው።"* (ገላ. 3፥11)

## ***ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 7***

## ***ሕግ እና የተስፋው ቃል፤ ገላ. 3፥15-22***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ጽድቅ የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ በሕግ አለመሆኑና ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን በመሆን ከሕግ ርግማን እንደ ዋጀን ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ አማኞች በዝርዝር ማስረዳቱን ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ከባለፈው በመቀጠል ጽድቅ የሚገኘው ሕግ በመጠበቅ እንዳልሆነ፣ እንዲሁም ለአብርሃም የተገባው የተስፋ ቃል በክርስቶስ በኩል እንደ ተፈጸመና ሕጉ ተስፋ የተደረገበት ዘር እስኪመጣ ድረስ በጊዜያዊነት እንዳገለገለ እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ቁጥር 15 ን በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ *"የሰው ስንኳ ቢሆን"* ብሎ ስለ ኪዳን የጠቀሳቸውን ነጥቦች አብራሩ።
2. በቁጥር 16 *"ለአብርሃምና ለዘሩም"* ተብሎ የተነገረው የተስፋ ቃል ማነው?
3. በቁጥር 17 *"ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተረጋገጠውን ኪዳን የተስፋውን ቃል እስኪሽር ድረስ አያፈርስም"* የሚለውን ሙሉ ሐሳብ አብራሩ።
4. ከቁጥር 18 እስከ 20 በማንበብ *"ርስቱ በሕግ ቢሆንስ እንግዲያስ በተስፋ ቃል አይሆንም"* ከሚለው ርስቱ ምን እንደ ሆነ፣ *"እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው?"* ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ የጠየቀውን እና *"መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም"* የሚሉትን ሐሳቦች አብራሩ።
5. በቁጥር 21 እና 22 መሠረት ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የማይቃወም ከሆነ ጽድቅ ከሕግ ያልሆነው ለምን ይመስላችኋል?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- በብሉይ ኪዳን ዘመን የተሰጡት ሁሉም ሕጎች በአዲስ ኪዳን ተሽረዋል ብላችሁ ታምናላችሁ? የብሉይ ሕግ ሙሉ በሙሉ ስላልተሻረ ለመጽደቅ በክርስቶስ ከማመን በተጨማሪ ሕግን መጠበቅ ወይም ልዩ ልዩ መልካም ሥራዎችን መሥራት እንደሚያስፈልግ ለሚያምኑ መልሳችሁ ምንድን ነው?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የተስፋ ቃል በክርስቶስ ኢየሱስ ፈጽሞታል። እኛም ይህን ጽድቅ ያገኘነው በሕግ ሳይሆን እግዚአብሔር ከዘመናት አስቀድሞ በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ብቻ ነው። በመሆኑም በእግዚአብሔር የተረጋገጠውን ኪዳን የተስፋውን ቃል እርሱም በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የጽድቅ ርስት ተቀብለናል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል።"* (ገላ. 3፥22)

## ***ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 8***

## ***የእግዚአብሔር ልጅነት (ክፍል 1)፤ ገላ. 3፥23-29***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሕግ በክርስቶስ በማመን ወደሚገኘው የመዳን መንገድ የሚወስድ ጊዜያዊ ሞግዚት ሆኖ እንዳገለገለ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን የእግዚአብሔር ልጅነታችንና የአብርሃም የተስፋ ቃል ወራሾች መሆናችንን እንዲሁም እኛ አማኞች በክርስቶስ ያለንን አንድነት እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 23-25 መሠረት የሕግ ሞግዚትነት አገልግሎት የቀጠለው እስከ መቼ ድረስ ነበር? *"ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም"* ማለትስ ምን ማለት ነው?
2. በቁጥር 26 መሠረት ክርስቶስን ማመናችን ምን ምን እንድንሆን አስቻለን?
3. በቁጥር 27 *"ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችሁታልና"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. በቁጥር 28 ላይ ጳውሎስ "የለም" እያለ የሚጠቅሳቸውን በመዘርዘር ሊይስተላልፍ የፈለገውን መልእክት ተወያዩ።
5. በቁጥር 29 መሠረት የክርስቶስ በመሆናችን ከአብርሃም ጋር ያለን ዝምድና ምንድን ነው? የምንወርሰውስ ተስፋ ምንድን ነው?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ማንነታችን የሚወሰነው በሕግ ወይም በሌሎች ውጪያዊ ሁኔታዎች ሳይሆን ኢየሱስ ከርስቶስን በማመን ባገኘነው የእግዚአብሔር ልጅነት መሆኑን ምን ያህል ተገንዝበናል? በዚህ ዘመን ዘርን፣ ቀለምን፣ ቋንቋንና የኑሮ ደረጃን መሠረት በማድረግ በቤተ ክርስቲያንም ይሁን በውጪ ለሚንጸባረቁ ልዩነቶች መፍትሔው ምን ይመስላችኋል?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን የእግዚአብሔር ልጆችና የተስፋው ቃል ወራሾች ሆነናል። እንግዲህ እግዚአብሔርን አባታችን ብለን ልንጠራው የሚያስችል የልጅነት ሥልጣንና ሰማያዊ ዜግነት ስለ ተቀበልን ምድራዊ ልዩነቶቻችንን ትተን ይህንን አንድነት የመጠበቅ መንፈሳዊ ኀላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና"* (ገላ. 3፥26)

## ***<u>ወደ ገላቲያ ሰዎች ጥናት 9</u>***

## ***<u>የእግዚአብሔር ልጅነት (ክፍል ሁለት)፤ ገላ. 4፥1-7</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን የእግዚአብሔር ልጅነታችንንና የአብርሃም የተስፋ ቃል ወራሾች መሆናችንን እንዲሁም እኛ አማኞች በክርስቶስ ያለንን አንድነት አይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ከሕግ ባርነት ነጻ ከመውጣታችን አልፎ በእምነት በክርስቶስ ኢየሱስ ባገኘነው የልጅነት መብት የእግዚአብሔር ወራሾች መሆናችንን እንመለከታለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 1-3 መሠረት ከጠባቂዎችና ከመጋቢዎች በታች መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
2. በቁጥር 4 እና 5 መሠረት *"ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ"* ሲል ምን ማለት እንደ ሆነ አብራሩ።
3. ቁጥር 5 እንደሚናገረው ኢየሱስ የመጣው ከሕግ በታች የነበርነውን ሊዋጅ ነው። ይህ ለእኛ ለአማኞች ምን ትርጉም አለው?
4. በቁጥር 6 መሠረት እግዚአብሔር ወደ ልባችን የላከው ምንድን ነው? ይህንን ያደረገውስ ለምን ይመስላችኋል?
5. በቁጥር 7 መሠረት የእግዚአብሔር ልጅነትን እና የእግዚአብሔር ወራሽ መሆንን መረዳት በሕይወታችን የሚያሳድረው ተጽእኖ ምንድን ነው?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- የእግዚአብሔር ልጅ በመሆን አባ አባት ብለን እግዚአብሔርን መጥራት መቻል ከሁሉ እጅግ የላቀ መታደል እንደ ሆነ ምን ያህል ተረድተሃል/ሻል?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

በክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣንና የተስፋው ቃል ወራሾች ልንሆን ተጠርተናል። ከሕግ ባርነትና ከሚያስከትለውም ፍርድ ነጻ ወጥተን አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀብለናል።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።"* (ገላ. 4፥ 6)

## ***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 10***

## ***ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የነበረው ናፍቆት፤ ገላ. 4፥8-20***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት በክርስቶስ በኩል ከሕግ ባርነት ነጻ ከመውጣታችን አልፎ በእምነት በክርስቶስ ኢየሱስ ባገኘነው የልጅነት መብት የእግዚአብሔር ወራሾች መሆናችንን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የገላትያ አማኞች ከወንጌል እውነት ፈቀቅ ማለታቸው ሐዋርያው ጳውሎስን እንደሚያሳስበውና መጀመሪያ ይዘውት ወደ ነበረው ትክክለኛ አስተምህሮ ተመልሰው ክርስቶስ ዳግም በውስጣቸው ተስሎ ሊያይ እንደሚናፍቅ ሲመክራቸው እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 8 *"ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁ"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።
2. በቁጥር 9-11 መሠረት የሐዋርያው ጳውሎስ ስጋት ምን ነበር?
3. በቁጥር 12 ጳውሎስ *"እኔ ደግሞ እንደ እናንተ ሆኛለሁና። እንደ እኔ ሁኑ ብዬ እለምናችኋለሁ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ከቁጥር 13 እስከ15 ስናነብ ሐዋርያው ጳውሎስ የሥጋ ድካሙን (አካላዊ ሕመሙን) መናገር የፈለገው ለምን ይመስላችኋል?
5. ከቁጥር 16–20 ላይ የገላትያ አማኞችን በብርቱ የሚፈልጉ ሰዎች ዐላማ ምንድን ነው? የሐዋርያው ጳውሎስስ ምጥ ምን ነበር?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ዛሬስ በሐሰተኛ አሰተማሪዎች በመታለል መጀመሪያ ከሰማነው እውነተኛ ወንጌል ፈቀቅ እንዳንል ምን ማድረግ ይገባናል?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን ተሸጋግረናል። በመሆኑም በየዘመኑ በሚነሱ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሐሰት ትምህርት በመታለል በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሥራ የተዋጀንበትን የከበረ ሕይወት እንዳንጥል በተመሠረትንበት እውነተኛ የወንጌል ትምህርት እስከ መጨረሻው ጸንተን ልንቆም ይገባናል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ልጆቼ ሆይ፥ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዘኛል።"* (ገላ. 4፥19)

## *ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 11*

## *የአጋር እና የሣራ ምሳሌነት፤ ገላ. 4፥ 21-31*

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት የገላትያ አማኞች ከወንጌል እውነት ፈቀቅ ማለታቸው ሐዋርያው ጳውሎስን እንደሚያሳስበውና መጀመሪያ ይዘውት ወደ ነበረው ትክክለኛ አስተምህሮ ተመልሰው ክርስቶስ ዳግም በውስጣቸው ተስሎ ሊያይ እንደሚናፍቅ ሲመክራቸው አይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ አጋር እና ሣራን እንደ ምሳሌ በመጠቀም ስለ ሁለቱ ኪዳኖች ያስረዳበትን በዝርዝር እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 21 *"እናንተ ከሕግ በታች ልትኖሩ የምትወዱ ሕጉን አትሰሙምን?"* በማለት የሚሞግተው ማንን እንደ ሆነ እና ለምን እንደ ሆነ ተወያዩ።
2. በቁጥር 23 *"ነገር ግን የባሪያይቱ ልጅ እንደ ሥጋ ተወልዶአል፥ የጨዋይቱ ግን በተስፋው ቃል ተወልዶአል"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. በቁጥር 24-27 መሠረት *"እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ኪዳኖች ናቸውና"* ሲል ምን ማለት ነው?
4. ከቁጥር 28 እስከ 31 በማንበብ በሥጋ ልጆችና በተስፋ ልጆች መካከል ያለውን ልዩነት በዝርዝር ተወያዩ።
5. በቁጥር 31 *"ስለዚህ ወንድሞች ሆይ የጨዋይቱ ልጆች ነን እንጂ የባሪያይቱ አይደለንም"* በማለት አማኞች የማን ልጆች እንደ ሆኑ የሚናገረው ሐሳብ ለእኛ የሚያስተላልፈውን መልእክት ምንድን ነው?

### *ከሕይወት ጋር ማዛመድ*

- እኛ የተስፋ ቃል ልጆች መሆናችን የሚሰጠን ትርጉም ምንድን ነው?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### *ማጠቃለያ*

አብርሃም አንዱ ከባሪያይቱ አንዱ ከጨዋይቱ የተወለዱ ሁለት ዐይነት ልጆች ነበሩት። እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ኪዳኖች ናቸው። አጋር በሕግ ላይ የተመሠረተውን አሮጌውን ኪዳንና ምድራዊዋን ኢየሩሳሌም ስትወክል ሣራ ደግሞ አዲሱን ኪዳንና ሰማያዊዋን ኢየሩሳሌም ትወክላለች። እኛ አማኞች የተስፋ ቃል፣ የጨዋይቱ ልጆች ነን።

### *በቃል የሚጠና ጥቅስ*

*"እኛም፥ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ይስሐቅ የተስፋ ቃል ልጆች ነን።"* (ገላ. 4፥28)

## ***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 12***

## ***በነጻነት ጸንቶ መኖር (ክፍል አንድ)፤ ገላ. 5፥1-7***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ አጋር እና ሣራን እንደ ምሳሌ በመጠቀም ስለ ሁለቱ ኪዳኖች ያስረዳበትን በዝርዝር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በክርስቶስ ነጻ ስለ ወጣን ተመልሰን በኃጢአት ባርነት ቀንበር እንዳንያዝ እንዴት ጸንተን መኖር እንዳለብን የመከረበትን እውነት በዝርዝር እንዳስሳለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 1 መሠረት በነጻነት እንድንኖር ነጻ ያወጣን ማን ነው? ነጻ የወጣነውስ ከምንድን ነው?
2. በቁጥር 2-4 መሠረት ሕግን በመጠበቅ ለመጽደቅ መሞከር ችግሩ ምንድን ነው?
3. በቁጥር 5 መሠረት በመንፈስ ከእምነት የምንጠብቀው የጽድቅ ተስፋ ምንድን ነው?
4. በቁጥር 6 መሠረት መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ የማይጠቅም ከሆነ የሚጥቅመው ምንድን ነው?
5. በቁጥር 7 መሠረት በገላትያ ይኖሩ የነበሩትን አማኞች ለእውነት እንዳይታዘዙ ያደረጋቸው ምን ነበር?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- በክርስቶስ ነጻ ወጥተን ሳለ አሁን ባለንበት ዘመን አማኞችን በባርነት ቀንበር ሊይዝ የሚችለው ምንድን ነው?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ድነትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ፊትም ጸድቀናል። ክርስቶስ ነጻ ስላወጣን ሕግን መጠበቅ ድነት የምናገኝበት መንገድ እንደ ሆነ ወይም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንድናገኝ እንደሚያደርግ በፍጹም ልናስብ አይገባም። ይህንን ካደረግን ለሕግ ባሪያ ሆነን ለድነታችን የእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ አያስፈልገንም እያልን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ነጻነትን በክርስቶስ አግኝተናል፤ ተመልሰን ወደ ባርነት ቀንበር እንዳንመለስ በእምነታችን ጸንተን መቆም የእኛ ነጻነቱን የተቀበልነው ሰዎች ኀላፊነት ነው።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።"* (ገላ. 5፥1)

## ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 13

## በነጻነት ጸንቶ መኖር (ክፍል ሁለት)፤ ገላ. 5፥8-15

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት በክርስቶስ ነጻ ስለ ወጣን በኀጢአት ባርነት ቀንበር ዳግም እንዳንያዝ እንዴት ጸንተን መኖር እንዳለብን ሐዋርያው ጳውሎስ የመከረበትን እውነት በዝርዝር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ባለፈው የጀመርነውን ተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ በማንሳት ተጨማሪ ቁም ነገሮችን እንማማራለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 8 ሐዋርያው ጳውሎስ *"ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል"* ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
2. በቁጥር 12 *"የሚያውኩአችሁ ይቆረጡ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. በቁጥር 13 *"አርነታችን ለሥጋ ምክንያት አይስጥ"* ሲል ምን ማለቱ ነው? *"እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ"* ማለቱስ?
4. በቁጥር 14 ሐዋርያው ጳውሎስ *"ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና"* በማለት የገለጸው የቱን ሕግ ነው?
5. በቁጥር 15 መሠረት የእርስ በርስ ጥላቻ የመጨረሻ ውጤቱ ምንድን ነው?

### *ከሕይወት ጋር ማዛመድ*

- ከሕግ ነጻ ወጥቶ በክርስቶስ ለአርነት እንደ ተጠራ ሰው ለወገኖች ያለን ፍቅር ምን ያህል ነው?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### *ማጠቃለያ*

እውነተኛ ነጻነት ማለት በአጭሩ ክርስቶስ በገለጠልን ፍቅር ጸንቶ መኖር ማለት እንደ ሆነ ተረድተን በዚህ ፍቅር ልንመላለስ ይገባል።

### *በቃል የሚጠና ጥቅስ*

*"ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።"* (ገላ. 5፥13)

## ***<u>ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 14</u>***

## ***<u>የሥጋና የመንፈስ መቀዋወም፤ ገላ. 5፥16-26</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ነጻ ስላወጣን ዳግም በባርነት ቀንበር መያዝ እንደሌለብን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የሥጋን ምኞት ባለ መፈጸም በመንፈስ መመላለስ እና የመንፈስ ፍሬ ማፍራት እንደሚኖርብን እናያለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 16 በመንፈስ እንዲመላለሱ ካዘዛቸው በኋላ በቁጥር 17 እና 18 መሠረት በመንፈስና በሥጋ መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? በሁለቱ መካክል ያለው ጦርነት በሕይወታችን ምን ያስከትላል?
2. ከቁጥር 19-21 ላይ የቀረቡትን የሥጋ ሥራዎች በመዘርዝር የሚያሰከትሉትን ውጤቶች ተወያዩ።
3. በቁጥር 22 እና 23 ላይ የቀረቡትን የመንፈስ ፍሬዎች በመዘርዘር የሚያሰከትሉትን ውጤቶች ተወያዩ።
4. በቁጥር 24 *"የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ"* ሲል ምን ማለት ነው?
5. በቁጥር 25 እና 26 መሠረት በመንፈስ መኖርና በመንፈስ መመላለስ ማለት ምን ማለት ነው?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- ➢ ዛሬ በሕይወታችን ጎልተው የሚታዩት የሥጋ ፍሬዎች ናቸው ወይስ የመንፈስ ፍሬዎች? ብለን በመጠየቅ ራሳችንን እንመርምር፤ ከቡድን አባላት ጋርም እንወያይ።
- ➢ በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ሰው ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስን ወደ ሕይወቱ በሚጋብዝበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያድራል፤ አዲስ ማንነትንም በውስጡ ይፈጥራል። መንፈስ ቅዱስ እኛ አማኞች እግዚአብሔርን ደስ የሚያስኝ ሕይወት እንዲኖረን ይፈልጋል። ነገር ግን አሮጌው ማንነታችን አሁንም ከእኛ ጋር ስላለ ኀጢአትን ማደርግ ይፈልጋል። በዚህም ምክንያት በአማኞች ሕይወት ጦርነት ይካሄዳል። የድል ሕይወት እንዲኖረን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘዉን ነገር ብቻ በአእምሯችንና በዐይኖቻችን ፊት በማስቀመጥ በመንፈስ በመመላለስ የሥጋን ፈቃድ መግደል ይጠበቅብናል።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።"* (ገላ. 5፥16)

## ***<u>ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 15</u>***

## ***<u>የደከመውን ማቅናት፤ ገላ. 6፥1-6</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት በመንፈስ በመመላለስ የመንፈስ ፍሬ ማፍራት እንደሚጠበቅብን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ መንፈሳዊ የሆነ ሰው አንድን በመንፈሳዊ ድካም ውስጥ የሚገኝን ሰው እንዴት ማቅናት እንዳለበት ሐዋርያው ጳውሎስ የሰጠውን ምክር እናያለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 1 መሠረት አንድ ሰው በማናቸውም በደል ቢገኝ መንፈሳዊ የሆነው ሰው የደከመውን ወገን እንዴት መርዳት ይጠበቅበታል?
2. በቁጥር 2 ሐዋርያው ጳውሎስ *"ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. በቁጥር 3 መሠረት ሰው ራሱን ሊያታልል የሚችለው እንዴት ነው?
4. በቁጥር 4 እና 5 መሠረት ሰው ራስን ከማታለልስ ማምለጥ የሚችለው እንዴት ነው?
5. በቁጥር 6 *"ቃሉን የሚማር ከሚያስተምረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ይከፋፈል"* ሲል ምን ማለት ነው?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- በመንፈሳዊ ድካም ያሉ ወገኖችን ስንመለከት እንዴት ልንረዳቸው እንደሚገባ ከዛሬው ክፍለ ምንባብ የተማራችሁትን እውነት ለቡድናችሁ አካፍሉ።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

በቅዱሳን ኅብረት መካከል አንድ ሰው በየትኛውም ዐይነት መንፈሳዊ ድካም ውስጥ ቢገኝ ዝም ብሎ ማየት ወይም መፍረድ ተገቢ አይደለም። ቃሉ እንደሚለው መንፈሳዊያን የሆንን ወገኖች በየውሃት መንፈስ ልናቀናው ይገባል። እኛም ብንሆን *ሥጋ* ለባሽ ሰዎች ስለ ሆንን በድካም ውስጥ ልንገኝ ስለምንችል ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥንቃቄ ማደረግ ይገባናል።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"ወንድሞች ሆይ፥ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፥ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት።"* (ገላ. 6፥1)

## ***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 16***

## ***የዘሩትን ማጨድ፤ ገላ. 6፥7-10***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት መንፈሳዊ የሆነ ሰው አንድን በመንፈሳዊ ድካም ውስጥ የሚገኝን ሰው እንዴት ማቅናት እንዳለበት ሐዋርያው ጳውሎስ የመከረበትን ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *"አትሳቱ … ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና"* ብሎ ያሳሰበበትን ክፍል በዝርዝር እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 7 ጳውሎስ *"አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. በቁጥር 7 *"ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና"* ይላል። የእግዚአብሔር ምሕረት የዘሩትን ከማጨድ የሚያስመልጥ ይመስላችኋል?
3. ቁጥር 8 ን በማንበብ ከሥጋ መበስበስን ማጨድ እና ከመንፈስ የዘላለም ሕይወትን ማጨድ በሚለው ሐሳብ ዙርያ ተወያዩ።
4. በቁጥር 9 መሠረት ሳንዝል ወይም ሳንታክት መልካም ሥራን መሥራት ያለብን ለምንድን ነው?
5. በቁጥር 10 መሠረት መልካም ማድረግ ያለብን ለማን ነው?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- የምንዘራውን ዘር እንጂ ዘሩን ከዘራን በኋላ የዘሩን ውጤት መቆጣጠር እንደማንችል የተረዳችሁትን ለቡድናችሁ አጋሩ።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ሁሉም አማኝ በመዝራትና በማጨድ መካከል ያለው ግንኙነት ቀጥተኛ መሆኑን ሊረዳ ይገባል። ሰው ከዘራው ነገር የተለየ ውጤት መጠበቅ አይኖርበትም። እኛ ሁላችን መልካም ሥራን መሥራት ትክክል እንደ ሆነ ማወቅ ብቻ ሳይሆን መልካም ዘር በመዝራት መልካሙን ነገር ለማጨድ መትጋትም ይጠበቅብናል። ዘር የምንዘራውም በሐሳባችን፣ በንግግራችን፣ በግንኙነቶቻችንና በየዕለቱ በምንኖረው ተግባራዊ ሕይወት ነው። ዛሬ በዘር ወቅት የምንዘራውን ወደ ፊት በመከር ወቅት በዝቶ የምናጭደው ከሆነ ሳንታክት መልካም ዘር መዝራት ይገባናል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና።"* (ገላ. 6፥7)

# ***ወደ ገላትያ ሰዎች ጥናት 17***

## ***ሌላ ትምክህትን ማራቅ፤ ገላ. 6፥11-18***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ *"አትሳቱ … ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና"* በማለት ያሳሰበበትን በዝርዝር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ አዲስ ፍጥረት ለመሆን ከክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህትን ማራቅ እንደሚገባ እናያለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 11 ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *"እንዴት ባሉ ታላላቆች ፊደላት በእጄ እንደ ጻፍሁላችሁ እዩ"* ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
2. በቁጥር 12 እና 13 መሠረት በሥጋ መልካም ሆነው ሊታዩ የሚወዱ ምን ዐይነት ሰዎች ናቸው?
3. በቁጥር 14 ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *"ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።
4. በቁጥር 15 እና 16 መሠረት በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆን ዋና ጠቃሚ ነገር የሆነው ለምን ይመስላችኋል? መገረዝም ሆነ አለመገረዝ ጠቃሚ ያልሆኑት ለምንድን ነው?
5. በቁጥር 17 ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *"እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያድክመኝ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ዛሬ በዚህ ዘመን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ከሕይወታችን ልናርቀው የሚገባ ሌላ ትምክህት ምን ምን ሊሆን ይችላል?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ የሚደርስበትን መከራና ስደት ሳይፈራ መገረዝም ሆነ ሌላ ውጫዊ ሥርዐቶችን በመፈጸም ከእግዚአብሔር ጋር እርቅ ማድረግ እንደማይቻል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የድነት መንገድ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስን በመቀበል አዲስ ፍጥረት መሆን እንደሚቻል አስረግጦ አስተምሯል። ዛሬም እያንዳንዳችን መከራን በመፍራት ወይም በሌሎች ምክንያቶች በእግዚአብሔር ቃል ላይ አንዳች መጨመርም ሆነ መቀነስ አይገባንም። ከክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ቢኖር ልናስወግድ ይገባናል። አዲስ ፍጥረት የሆንነው በመስቀሉ ሥራ ነውና።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና። "*(ገላ. 6፥15)

## የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች

**መግቢያ**

የኤፌሶን መልእክት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሮም እስር ቤት ከጻፋቸው አራት ደብዳቤዎች መካከል አንዱ ነው (ቀሪዎቹ ሦስቱ ደብዳቤዎች፤ ፊልጵስዩስ፣ ቈላስይስ እና ፊልሞና ናቸው)። በዚህ ደብዳቤ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ሠፊ ትኩረት ከመስጠቱ የተነሣ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል ዘጠኝ ጊዜ ተጠቅሷል። ዐውዱን በጠበቀ መልኩ የደብዳቤውን ይዘት ለመወያየት ይረዳን ዘንድ የደብዳቤውን ታሪካዊ ዳር እንደሚከተለው በአጭሩ በመዳሰስ እንጀምራለን።

**ጸሐፊ**፤ የኤፌሶን መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ መሆኑ በመልእክቱ መግቢያ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፤ *"በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ"*(1÷1) ይላል። ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን ሲጽፍ በእስር ላይ እንደ ነበረ በመልእክቱ ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል (3÷1፤ 4÷1፤ 6÷19-20)። በጥቅሉ የደብዳቤው መግቢያ፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ምስክርነት፣ የደብዳቤው ቅርጽና ነገረ መለኮታዊ ይዘት ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ለመሆኑ እንደ ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀርቡ ይችላሉ።

**ተቀባይ**፤ የደብዳቤው ተቀባዮች በኤፌሶን የነበሩ ቅዱሳን መሆናቸውን ከደብዳቤው የመክፈቻ ቁጥር መረዳት ይቻላል፤ *"በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን በክርስቶስ ኢየሱስም ላሉት ምእመናን"*(1÷1) ይላል። ኤፌሶን ቀድሞ ትንሿ እስያ በመባል በምትታወቀው በአሁኗ ቱርክ ውስጥ የምትገኝ ከተማ ነች። ይህች ከተማ በባሕር ተከበ የምትገኝ በመሆኗ ከወደብነት ባለፈ ታላላቅ የንግድ መስመሮች የሚተላለፉባት እና አርጤምስ በምትባል የጣዖት አምልኮም የምትታወቅ ከተማ ነበረች። ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ከተማ የወንጌል ሥርጭት ማእከል በማድረግ ለሦስት ዓመት ያህል በዚያ እንደ ቆየ ይታወቃል (የሐዋ. 19፥1-20፥31)።

**የተጻፈበት ጊዜና ቦታ**፤ ይህ ደብዳቤ በ61/62 ዓ.ም አካባቢ ከሮም እስር ቤት እንደ ተጻፈ በብዙዎች ዘንድ ይታመናል። ደብዳቤው ከቈላስይስ እና ከፊልሞና መልእክቶች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ተጽፎ በቲኪቆስ በኩል እንደ ተላከም ብዙዎች ይናገራሉ።

**የመልእክቱ ዐላማ**፤ የኤፌሶን መልእክት እንደ አንዳንድ የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች የተወሰኑ የሐሰት ትምህርቶችንና ልምምዶችን ለማረም የተጻፈ መልእክት አይደለም። ይልቁንም አማኞች እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያደረገላቸውን እና ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ሰማያዊ ዕቅድ፣ ከምእራፍ 1 እስከ 3 የተጻፈውን እውነት በመረዳት ይህንን ጥሪ በሚመጥን ምድራዊ ኑሮ፣ ከምዕራፍ 4 እስከ 6 እንደ ተጻፈው መንፈሳዊ አካሄድ እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባቸው ለማስረዳት ነው። በሌላ አገላለጽ መልእክቱ የተጻፈው አማኞች የእግዚአብሔርን የዘላለም ዕቅድና ሐሳብ እንዲሁም የፍቅሩንና የጸጋውን ሥፋትና ጥልቀት በመረዳት ተግባራዊ በሆነ የክርስትና ሕይወት እንዲመላለሱ ለማሳሰብ ነው።

## ***<u>ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 1</u>***

## ***<u>በክርስቶስ ያገኘነው በረከት፤ ኤፌ. 1÷1-8</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

የኤፌሶንን መልእክት በምንጀምርበት በዛሬው ጥናታችን እግዚአብሔር በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ እንደ ባረከን እና ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ እንደ መረጠን እንመለከታለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 1 ላይ *"በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ"* ሲል ምን ማለቱ ነው? ጳውሎስ በመጀመሪያ ቁጥር ይህን መግለጽስ ለምን አስፈለገው?
2. ቁጥር 3 ን መሠረት በማድረግ እግዚአብሔር አብ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት እንዴት እንደ ባረከን ተወያዩ።
3. በቁጥር 4 *"ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን"* የሚለው ሐሳብ ምን ማለት እንደ ሆነ ተወያዩ (ለተጨማሪ ንባብ ሮሜ 8÷29 እና ቈላ. 1÷19 ን ይመልከቱ)።
4. በቁጥር 5 እና 6 መሠረት አማኞች የልጅነት ሥልጣን እንዴት እና ለምን እንዳገኙ በመግለጽ ተወያዩ።
5. ቁጥር 7 እና 8 በማንበብ በደሙ በተደረገው ቤዛነት የኀጢአት ይቅርታ ማግኘታችን የእግዚአብሔርን ጸጋ ባለ ጠግነት እንዴት እንደሚያሳይ ተነጋገሩ (ለተጨማሪ ንባብ ቈላ.1÷14 ን ተመልከቱ)።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- እግዚአብሔር በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ እንደ ባረከን እና ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ እንደ መረጠን መገንዘባችን በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ላይ ምን ያህል ለውጥ ሊፈጥር እንደሚችል የተረዳኸውን/ሽውን አካፍል/ይ።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

የዘላለም አምላክና የፍጥረት ሁሉ ምንጭ የሆነው እግዚአብሔር አባታችን አስቀድሞ በወሰነው መሠረት በልጁ በኩል መረጠን። ለመረጠን ለእኛ በመንፈሳዊ ስፍራ መንፈሳዊ በረከትን አዘጋጀልን። እኛም ክቡር በሆነው በልጁ ደም የተዋጀን እንደ መሆናችን መጠን በእምነታችን ጸንተን ሁልጊዜ ለእግዚአብሔርና ለጸጋው ክብር ምስጋናን ማቅረብ ይገባናል።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።"* (ኤፌ.1፥3)

## ***<u>ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 2</u>***

## ***<u>ሁሉ በክርስቶስ መጠቅለሉና በመንፈስ ቅዱስ መታተማችን፤ ኤፌ. 1÷9-14</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት እግዚአብሔር በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ እንደ ባረከን እና ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ እንደ መረጠን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እግዚአብሔር አብ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉን ሊጠቀልል እንደ ወደደና እንዲሁም አማኝ ጌታን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል በመንፈስ ቅዱስ ታትሞ የልጅነት መብት እንደሚጎናጸፍ ያስረዳበትን እናያለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 9 *"በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ አሳቡ፥ የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና"* ይላል፤ ለመሆኑ የፈቃዱ ምሥጢር ምን ይመስላችኋል?
2. በቁጥር 10 *"በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው"* የሚለው ሐሳብ ምን ማለት እንደ ሆነ ተወያዩ።
3. በቁጥር 11 እና 12 መሠረት በክርስቶስ የተቀበልነው ርስት ምን እንደ ሆነና ይህንንም ርስት የመቀበላችን ዐላማ ለምን እንደ ሆነ በማብራራት ተወያዩ።
4. በቁጥር 13 *"እናንተ ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ"* ሲል ምን ማለት እንደ ሆነ አብራሩ። (ለተጨማሪ ማብራሪያ 2ኛ ቆሮ. 1፥21-22 እና ቲቶ 3፥5 ን አንብቡ)።
5. በቁጥር 14 ላይ መንፈስ ቅዱስን *"እርሱም የርስታችን መያዣ ነው"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ። (ለተጨማሪ ማብራሪያ 2ኛ ቆሮ. 5÷5 ን ማንበብ ትችላላችሁ)።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- የእግዚአብሔር ባለ ቤትነት ምልክት በሆነው በመንፈስ ቅዱስ መታተማችን እና ለእኛም የምንወርሰውን ርስት አስተማማኝ የሚያደርግ መያዣ መንፈስ ቅዱስን መሰጠቱ ምን ያህል ዕለት ዕለት ደስ ያሰኘናል?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

የእውነትን ቃል፥ ይኸውም የመዳናችንን ወንጌል፥ ሰምተን በክርስቶስ ስናምን፥ የእግዚአብሔር ባለ ቤትነት ምልክት በሆነው በመንፈስ ቅዱስ መታተማችን (God's Seal)፣ የምንወርሰውን ርስት አስተማማኝ የሚያደርግ መያዣ (Like Security Deposit) መንፈስ ቅዱስን መቀበላችን እና እግዚአብሔር በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል መሆኑ በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ"* (ኤፌ.1፥13)

## ***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 3***

## ***የምስጋናና የልመና ጸሎት፤ ኤፌ. 1፥15-23***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት እግዚአብሔር አብ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉን ሊጠቀልል እንደ ወደደና ማንኛውም አማኝ ጌታን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል በመንፈስ ቅዱስ ታትሞ የልጅነት መብት እንደሚጎናጸፍ ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶን አማኞች በጌታ ኢየሱስ ስላላቸው እምነት እና ለቅዱሳን ሁሉ ስላላቸው ፍቅር ሰምቶ እግዚአብሔርን እንዴት እንዳመሰገነ እና የኀይሉን ታላቅነት እንዲያውቁ፣ እንዲሁም የልባቸው ዐይኖች በጥበብ እንዲከፈቱ የጸለየላቸውን ጸሎት እንዳስሳለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 15 እና 16 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ኤፌሶን ቅዱሳን ሰምቶ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት ምክንያት ምን ነበር?
2. ከቁጥር 17 እስከ 19 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ለነበሩ ቅዱሳን የጸለየላቸውን የጸሎት ርእሶች በመዘርዘር የእያንዳንዱን ርእስ አስፈላጊነት/ጠቃሚነት ተነጋገሩ።
3. በቁጥር 17 ላይ እግዚአብሔር የተገለጸው እንዴት ነው? ይህ ገለጻስ ምን ያስተምራል?
4. በቁጥር 20 እና 21 እግዚአብሔር አብ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳበትና ከጌትነትም ሁሉ በላይ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ያስቀመጠበት ምክንያት ምንድን ነው?
5. ቁጥር 22 እና 23 ን በማንበብ ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ መሆኑና ቤተ ክርስቲያን አካሉና ሙላቱ መሆኗ ምን ዐይነት መንፈሳዊ ፋይዳ እንዳለው ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ስለ ነበሩ ቅዱሳን በሰማው ምስክርነት በመደሰቱ ምን ያህል እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ ስንወያይ ዛሬ ላይ የእኛስ ምስክርነት ምን ይመስላል በማለት ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል። ሌላው ሐዋርያው የጸለየውን ጸሎት ዛሬም ለራሳችንና ለሌሎች መጸለይ ይኖርብናል። የቤተ ክርስቲያን ባለ ቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው!
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ዛሬም አማኞች በጌታ ላይ ባላቸው እምነትና ለሌሎች ባላቸው ፍቅር ሊታወቁ ይገባል። እንደ አማኞች ክርስቶስን በማወቅ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲበዛልን፣ የልባችን ዐይን በርቶ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን፣ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት እና ከሁሉ የሚበልጠው የኀይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ይበልጥ በማወቅ እንድናድግ ልንጸልይ ይገባል። ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውና ከስም ሁሉ በላይ ስም ያለው ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ወይም ዋና ባለ ቤት ነው።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።"* (ኤፌ. 1፥17)

## ***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 4***

## ***በክርስቶስ ሕያው መሆን፤ ኤፌ. 2÷1-10***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶን አማኞች በጌታ ስላላቸው እምነት እና ለቅዱሳን ሁሉ ስላሳዩት ፍቅር ሰምቶ እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ፣ እንዲሁም የኀይሉን ታላቅነት እንዲያውቁና የልባቸው ዐይኖች በጥበብ እንዲከፈቱ የጸለየላቸውን ጸሎት ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በበደላችንና በኀጢአታችን ሙታን በነበርንበት ጊዜ እግዚአብሔር ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በደሙ በተደረገ ቤዛነት የዘላለም ሕይወትን እንዲያው በነጻ እንዴት እንደ ሰጠን እናያለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 1 *"በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. በቁጥር 2 መሠረት በማይታዘዙት ልጆች ላይ የሚሰለጥንና፤ በአየር ላይ ያሉ ክፉ ኀይላት ገዢ ተበሎ የተጠቀሰው ማን ነው?
3. በቁጥር 3 መሠረት "የቁጣ ልጆች" ሊያስብለን የቻለው ምን ነበር?
4. ከቁጥር 4-7 በማንበብ በደለኞች ሆነን ሳለ እግዚአብሔር አብ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ከሁሉ የሚበልጠው የጸጋውን ብርታት እንዴት እንደ ገለጸው እና ይህ በሕይወታችን ላይ ያመጣው አዎንታዊ ተጽእኖ ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።
5. በቁጥር 8 *"ጸጋዉ በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም"* የሚለው ሐሳብ ምን ማለት እንደ ሆነ ተወያዩ። (በተጨማሪ ገላ. 2፥16 ን አንብቡ)

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- በእምነት የዳንበት ጸጋ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው እንጂ የእኛ *ሥራ* ውጤት አይደለም። ለመሆኑ በጌታችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል *ሥራ* ባገኘነው ምሕረት ምን ያህል ደስተኞችና አመስጋኞች ነን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እግዚአብሔር ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዲያው በጸጋው በእምነት አዳነን፤ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ ከሥራ አይደለም። ክርስቲያን መልካም *ሥራን* የሚሰራው ድነትን ስለ ተቀበለ እንጂ ገና ወደ ፊት ለመዳን አይደለም። ይህንንም ማወቃችን ለልባችን የማዳኑ ደስታ፣ ለነፍሳችን ሰላምና ፍጹም ዕረፍት ከማብዛቱም በላይ የፍቅሩን ጥልቀትና የጸጋውን ብዛት እያሰላሰልን እንድንደነቅና እንድንፍለቀለቅ ያደርገናል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም"* (ኤፌ. 2÷8)

## ***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 5***

## ***በክርስቶስ አንድ መሆን፤ ኤፌ. 2÷11-22***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት በበደላችንና በኀጢአታችን ሙታን በነበርንበት ጊዜ እግዚአብሔር ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በደሙ በተደረገ ቤዛነት የዘላለም ሕይወትን እንዲያው በነጻ እንዴት እንደ ሰጠን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እግዚአብሔር ከጸጋው ብዛት የተነሳ አስቀድሞ ለተስፋው ቃል እንግዶች የነበርነውን ለማቅረብ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ፣ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው አፍርሶ፣ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንዳስታረቀን እናያለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ቁጥር 11 እና 12 አስቀድመው በሥጋ አሕዛብ የነበሩትን በምን መልኩ ይገልጻሉ? በቁጥር 13 መሠረት አሁንስ ምን እንደ ሆኑ ይናገራል? ከክርቶስ ውጪ ያለ ሕይወት እና በክርስቶስ የድነት ሥራ በተገኘው ሕይወት መካከል ያለውን በማነጻጸር ተወያዩ።
2. ከቁጥር 14 እስከ 18 በማንበብ *"ሁለቱን ያዋሐደ …"* የሚለውን ሐሳብ በተለይም ሁለቱ የተባሉት እነማን እንደ ሆኑ እና ከሁለቱ ስለ ተፈጠረው አንድ አዲስ ሰው በስፋት ተወያዩ።
3. በቁጥር 19 መሠረት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተሠራው የድነት ሥራ አሕዛብን ምን እንዳደረገ ተወያዩ።
4. በቁጥር 20 *"በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. በቁጥር 21 ላይ ቤተ ክርስቲያን በሕንጻ መመሰሏ ምን ትምህርት ይሰጣል? ለተጨማሪ ማብራሪያ 1ኛ ቆሮ. 3÷11-17 ን ማንበብ ትችላላችሁ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት በመቻላችን በየዕለት በሕይወታችን የክርስቶስን ሰላም እንድንለማመደው ምን ያህል ረድቶናል? በክርስቶስ የመስቀል ሥራ በማመናችን በጸጋው የዳንን ሰዎች ብንሆንም ገና ተሠርተን የተጠናቀቅን ሕንጻዎች ስላልሆንን ወደ ክርስቶስ ሙላት እናድግ ዘንድ በየዕለቱ በእግዚአብሔር ለመሠራት ምን ያህል እንፈቅዳለን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እኛ ምንም እንኳ በበደላችንና በኀጢአታችን ከእርሱ ርቀን የነበርን ብንሆንም እግዚአብሔር እኛን ከራሱ ጋር ለማስታረቅ ያሳየውን ፍቅር ተቀብለን ከሌሎች አማኞች ጋር በአንድነት ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ አብረን እንድናድግ ተጠርተናል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና።"* (ኤፌ. 2÷14)

## ***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 6***

## ***የጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያነት፤ ኤፌ. 3÷1-13***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት እግዚአብሔር ከጸጋው ብዛት የተነሳ አስቀድሞ ለተስፋው ቃል እንግዶች የነበርነውን ለማቅረብ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ፣ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው አፍርሶ፣ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳስታረቀን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እግዚአብሔር በወንጌል አማካኝነት፣ የጸጋው ባለ ጸግነት ለሰው ልጆች ሁሉ ይሆን ዘንድ እንደ ገለጸና ይህንንም የምሥራች ወንጌል እንዲያበስር ሐዋርያው ጳውሎስን ወደ አሕዛብ ሁሉ እንደ ላከው እናያለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 1 መሠረት ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው በምን ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ነበር?
2. ቁጥር 2፣ 7-9 ን በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ የጸጋ ስጦታ የተሰጠው ለምን እንደ ሆነ አብራሩ።
3. በቁጥር 3-6 መሠረት አስቀድሞ ምሥጢር የነበር አሁን ግን የተገለጠ የሆነው ነገር ምን ነበር?
4. ከቁጥር 7 እስከ 9 በማንበብ አሕዛብ ከአይሁድ ጋር የጸጋው ወራሾች የሆኑት እንዴት እንደ ሆነ አብራሩ።
5. ከቁጥር 10 እስከ 13 በማንበብ የእግዚአብሔር ጥበብ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የተፈጸመው የዘላለም አሳብ፣ በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ እንዳለን የተነሡትን ነጥቦች ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ውስጥ እንዳለንና የጸጋው ተካፋዮች መሆናችንን ማወቃችን ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ዕድገት ምን ያህል ጠቃሚ እንደ ሆነ አብራሩ።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እግዚአብሔር ሐዋርያው ጳውሎስን ወደ አሕዛብ እንደ ላከው እኛንም ወደ ወደደው ሊልከን ይችላል። ሆኖም የአገልግሎት ማለፊያ ሁል ጊዜ አልጋ ባልጋ ሳይሆን እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ መንገዱ ሻካራም ሊሆን ይችላልና ለመታዘዝ እንዘጋጅ። እግዚአብሔርን በሙሉ ክብሩና ኀይሉ ማወቃችን እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ በልዩ ልዩ መከራ ብናልፍ እንኳ ጸንተን እንድንቆም ብርታት ይሆነናል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*“ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፥ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደ ሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ ተሰጠ”* (ኤፌ. 3÷9)

## *ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 7*

## *ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው ጸሎት፤ ኤፌ. 3÷14-21*

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት እግዚአብሔር በወንጌል አማካኝነት የጸጋው ባለ ጸግነት ለሰው ልጆች ሁሉ ይሆን ዘንድ እንደ ገለጸና ይህንንም የምሥራች ወንጌል እንዲያበስር ሐዋርያው ጳውሎስን ወደ አሕዛብ ሁሉ እንደ ላከው ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በአብ ፊት ተንበርክኮ በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታቸው በኀይል እንዲጠነክሩ፣ ክርስቶስም በልባቸው በእምነት እንዲኖር፣ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ይበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሰው ይሞሉ ዘንድ፣ የእነርሱም ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ የጸለየላቸውን ጸሎት እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከቁጥር 14 እስከ 17 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ በእስር ላይ ሆኖ በኤፌሶን ለነበሩ ቅዱሳን አጥብቆ የሚጸልየው ስለ ምን እንደ ሆነ በመዘርዘር ተወያዩ።
2. በቁጥር 18 እና19 የክርስቶስ ፍቅር የተገለጠው በምን መልኩ እንደ ሆነ ተነጋገሩ።
3. *"…ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ"* የሚለውን ገለጻ በማብራራት ተወያዩ።
4. በቁጥር 20 *"እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. በቁጥር 21 *"ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን"* ያለው ምን ሊያደርግ እንደሚችል ከገለጸ በኋላ ነው?

### *ከሕይወት ጋር ማዛመድ*

- በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችን በኀይል እንድንጠነክር፣ ክርስቶስም በልባችን በእምነት እንዲኖር፣ እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን እንዲሰጠን፣ የእኛ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ ምን ያህል በእግዚአብሔር ፊት እንንበረከካለን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### *ማጠቃለያ*

ጸሎት ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እንደ እስትንፋስ መሆኑን ተረድተን በእኛ እንደሚሠራው ኀይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ በሚችለው በእግዚአብሔር ፊት በእምነት ልንቀርብ ይገባል። እንዲሁም በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችን በኀይል እንድንጠነክር፣ ክርስቶስም በልባችን በእምነት እንዲኖር፣ እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን እንዲሰጠን፣ የእኛ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት በአብ ፊት ልንበረከክ ይገባል። እንግዲህ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

### *በቃል የሚጠና ጥቅስ*

*"ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ"* (ኤፌ. 3÷14-15)

## ***<u>ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 8</u>***

## ***<u>መንፈሳዊ አንድነት፤ ኤፌ. 4÷1-6</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ በውስጥ ሰውነታቸው በኀይል እንዲጠነክሩ፣ ክርስቶስም በልባቸው በእምነት እንዲኖር፣ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ይበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሰው ይሞሉ ዘንድ፣ እንዲሁም የእነርሱ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ የጸለየላቸውን ጸሎት ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በማይመች ሁኔታ በእስር ላይ ሆኖ እንኳ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር፣ ሰላምና አንድነት ጉዳይ ያሳስበው ስለ ነበር አማኞች የተጠሩበትን ጥሪ በሚመጥን ሕይወት እንደሚገባ ይመላለሱ ዘንድ ያስተላለፈውን መልእክት እንቃኛለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 1 ላይ *"... እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ"* ሲል ምን ማለቱ ነው? ሐዋርያው ማዘዝ እየቻለ መለመኑስ ምን ያስተምራል?
2. በቁጥር 2 መሠረት አማኞች ጥሪያቸውን በሚመጥን ደረጃ እንደሚገባ የመመላለሳቸው መገለጫዎች ሆነው የቀረቡት ምን ምንድን ናቸው?
3. በቁጥር 3 *"በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ከቁጥር 4 እስከ 6 በማንበብ የመንፈስ አንድነትን በትጋት ለመጠበቅ የሚረዱትን *"አንድ ..."* በማለት የቀረቡ ሰባት የአንድነት መሠረቶችን በመዘርዘር ስለ እያንዳንዱ ተወያዩ።
5. በቁጥር 6 ላይ እግዚአብሔር የተገለጸው እንዴት ነው?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- ከጌታ የተሰጠንን የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅ በግልም ይሁን በኅብረቶቻችን ምን ያህል እንተጋለን? በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ባሕርያትስ ምን ያህል በሕይወታችን እየተገለጡ ናቸው?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ሐዋርያው ጳውሎስ በእስር ላይ በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንኳ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር፣ ሰላምና አንድነት ምን ያህል እንዳሳሰበው ይህ ክፍለ ምንባብ ያሳያል። ሐዋርያው አማኞች የተጠሩበትን ጥሪ የሚመጥን ሕይወት እንዲኖሩ፣ በአግባቡ እንዲመላለሱ እንዴት እንደ መከራቸው ተመልክተናል። ይህ ጥሪ በኤፌሶን ለነበሩ ቅዱሳን ብቻ ሳይሆን ዛሬም ለእኛ በመሆኑ በክፍሉ በቀረቡ እውነቶች ላይ ተመሥርተን የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ልንተጋ ይገባናል።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ"* (ኤፌ. 4÷1)

## ***<u>ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 9</u>***

## ***<u>ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ የጸጋ ስጦታዎችና ዐላማቸው፤ ኤፌ. 4÷7-16</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር፣ ሰላምና አንድነት ጉዳይ ምን ያህል እንዳሳሰበውና አማኞች የተጠሩበትን ጥሪ የሚመጥን የሕይወት ምልልስ እንዲኖራቸው እንደ መከራቸው ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ወደደ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሰጠና የሰጠበትንም ዐላማ እንመለከታለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 7 *"... እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን"* ከሚለው በመነሣት እያንዳንዱ አማኝ ቢያንስ አንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳለው መናገር እንችላለን? መልሳችሁን ከነምክንያቱ በማቅረብ አብራሩ።
2. ከቁጥር 8 እስከ 10 በማንበብ ወደ ምድር ታችኛ ክፍል መውረድና ከሰማይ ሁሉ በላይ መውጣት የሚለው አገላለጽ ምን ማለት እንደ ሆነ ወይም ምንን እንደሚያሳይ ተወያዩ።
3. በቁጥር 11 ላይ የተጠቀሱትን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው ልዩ ልዩ ስጦታ ያላቸውን አገልጋዮች በዝርዝር በማቅረብ ስለ እያንዳንዱ አገልግሎት ተወያዩ።
4. በቁጥር 12 እና 13 መሠረት እነዚህ ልዩ ልዩ ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡት ለምን ዐላማ ነው?
5. ከቁጥር 14 እስከ 16 በማንበብ በመንፈሳዊ ዕድገታችን ወደ ፊት ሕፃናት መሆን የማይገባን ለምን እንደ ሆነና ማደግ ያለብን ደግሞ ወደ ማን እንደ ሆነ በዝርዝር ተነጋገሩ።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- በዛሬው ክፍለ ምንባብ በተወያየነው መሠረት ከጌታ ዘንድ የተቀበልነውን ቢያንስ አንድ መንፈሳዊ ስጦታ ለምን ዐላማ እያዋልነው ይሆን? በጌታ ቤት ከቆየነው ጊዜ አንጻር በምን ዐይነት የመንፈሳዊ ሕይወትብስለት ላይስ እንገኛለን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታ ተሰጥቶናል። ጌታ መንፈሳዊ ስጦታን ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ ስጦታ ያላቸውን አገልጋዮችንም ለቤተ ክርስቲያን ይሰጣል። ስጦታውም ሆነ ሰዎቹ የተሰጡበት ዐላማ ቤተ ክርስቲያንን ማነጽ ነው። መንፈሳዊ ስጦታዎች በትክክል ሲገለጹ ከሐሰት ትምህርት ተጠብቀን በነገር ሁሉ ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ እናድጋለን። ጌታ ይርዳን!

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን።"* (ኤፌ. 4÷7)

## ***<u>ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 10</u>***

## ***<u>ከንቱ አዕምሮና የታደሰ አዕምሮ፤ ኤፌ. 4÷17-24</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ እንደ ተሰጠን እንዲሁም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ እንደ ሰጠና የተሰጠበትም ዐላማ ምን እንደ ሆነ ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በኤፌሶን የነበሩ አማኞች በአእምሮ ከንቱነት መመላለስን አስወግደው በአእምሮ መታደስ እንዲሚገባቸው ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተላለፈላቸውን ምክር እንመለከታለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. ከቁጥር 17 እስከ 19 በማንበብ አሕዛብ እንደሚመላለሱ በአእምሮ ከንቱነት የመመላለስ ውጤቶች ሆነው የቀረቡትን በመዘርዘር ተወያዩ።
2. ከቁጥር 20 እስከ 22 በተጻፈው መሠረት በኤፌሶን የነበሩ ቅዱሳን የተማሩት (ምን ተማሩ) እና ሊያስወግዱት የሚገባውስ ምንድን ነው?
3. በቁጥር 23፣ “በአእምሮአችሁም መታደስ ታደሱ” ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ እና በምን መልኩ ይህን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ተወያዩ።
4. በቁጥር 24 መሠረት በኤፌሶን የነበሩ ቅዱሳን ሊለብሱት የሚገባቸው እና በእነርሱ ሕይወት ሊገለጡ የሚገቡ መንፈሳዊ ባሕርያት ምን ምን እንደ ሆኑ ከእኛ ሕይወት ጋር በማዛመድ ተወያዩ።
5. በቁጥር 24 ሐዋርያው ጳውሎስ፣ “አዲሱን ሰው ልበሱ” ሲል ምን ማለቱ ነው?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- ➢ ከክርስቶስ በፊት የነበረህን/ሽን የቀድሞ ሕይወት በክርስቶስ ከተለወጠው ከአዲሱ ማንነትህ/ሽ ጋር በማነጻጸር ለሌሎች ትምህርት በሚሰጥ መልኩ ምስክርነትህን/ሽን አካፍል/ይ።
- ➢ በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ዛሬ ሕይወታችን ምን ያህል ተለውጧል? ለውጣችንስ ከሌሎች ጋር ባለን የዕለት ተዕለት መስተጋብር ማለትም በቤታችን፣ በሥራ ቦታና በቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ምን ያህል የተገለጠ ነው? ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ለነበሩ ቅዱሳን እንዳሳሰበው እንደ አሕዛብ በአእምሮ ከንቱነት መመላለስን ወይም አሮገውን ማንነት ሙሉ በሙሉ አሽቀንጥረን በመጣል በአእምሮ መንፈስ መታደስ ይጠበቅብናል! ማስወገድ የሚገባንን ሁሉ እያስወገድን አዲሱን ሰው ልንለብስ/ልንገልጥም ይገባል!

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*“..አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ”* (ኤፌ. 4÷23)

## ***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 11***

## ***ቅዱሱን መንፈስ አታሳዝኑ፤ ኤፌ. 4÷25-32***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት የኤፌሶን አማኞች በአእምሮ ከንቱነት መመላለስን አስወግደው በአእምሮ መንፈስ መታደስ እንዲሚገባቸው ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተላለፈላቸውን ምክር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ አማኞች ለቤዛ ቀን የታተሙበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳያሳዝኑ ማድረግ ስለሚገባቸውና ስለማይገባቸውን ባሕርያት በዝርዝር እንነጋገራለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 25 *"ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ … "* ይላል፤ ውሸትን ማስወገድ የሚቻለው እንዴት ነው?
2. በቁጥር 26 እና 27 መሠረት አማኞች ቁጣቸው ለዲያቢሎስ ዕድል እንዳይሰጥ ምን ማድረግ አለባቸው?
3. በቁጥር 28 መሰረት አንድ ሰው ከስርቆት ተቆጥቦ እንደውም ለተቸገሩት ማካፈል ይችል ዘንድ ምን ማድረግ አለበት?
4. ከቁጥር 29 እስከ 31 በማንበብ አማኞች ለቤዛ ቀን የታተሙበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳያሳዝኑ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና እርስ በርሳቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸቸው ተወያዩ።
5. *"ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ"* የሚለው ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት ምን ያስተምራል?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ዛሬ ከሰማነው የእውነት ቃል በመነሳት ለቤዛ ቀን የታተምንበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳናሳዝን ምን ማስወገድ ይጠበቅብናል? እርስ በርሳችን ባለን ግንኙነትስ ምን ማድረግ ይኖርብናል?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

መንፈስ ቅዱስን እንደ ኀይል ብቻ ማሰብ ስህተት ነው፤ እርሱ ማንነት ያለው በመሆኑ የሚያዝን አምላክ ነው። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑ እኩይ ባሕርያትን ሁሉ በማስወገድ እርሱ የሚከብርባቸውን ሰናይ ባሕርያት ልንለማመድ/ልናሳይ ይገባል። ውሸትን አስወግደን እውነትን በመናገር፣ ችግሮቻችንን በመፍታት በቁጣችን ላይ ፀሐይ እንዳይገባ በማድረግ፣ ከሌሎች ከመስረቅ ይልቅ በገዛ እጆቻችን ሠርተን ለሌሎች በማካፈል፣ ከክፉ ቃል ይልቅ በጎ ቃል በመናገር፣ እርስ በርሳችን ቸሮች፣ ርኅሩኆች እና ይቅር የምንባባል በመሆኑ መንፈስ ቅዱስን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ልንኖር ይገባል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።"* (ኤፌ. 4÷30)

## ***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 12***

## ***እንደ ተወደዱ ልጆች መመላለስ፤ ኤፌ. 5÷1-7***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት አማኞች ለቤዛ ቀን የታተሙበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳያሳዝኑ ማድረግ ስለሚገባቸውና ስለማይገባቸው ባሕርያት በዝርዝር ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ስንከተል በሕይወታችን ሊታዩ ስለሚገባቸውና ስለማይገባቸው ባሕርያት በዝርዝር እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 1 እና 2 መሠረት *"እንደ ተወደዱ ልጆች"* ምን ዐይነት ተግባራዊ ሕይወት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተወያዩ።
2. ቁጥር 3 እና 4 ን በማንበብ እንደ ቅዱሳን በእነርሱ ዘንድ መታየት ወይም መሰማት የሌለባቸውን ነገሮች በዝርዝር በማቅረብ በእያንዳንዱ ላይ ተወያዩ።
3. በቁጥር 5 *"በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም"* የተባለው ምን የሚያደርግ ነው?
4. በቁጥር 6 መሠረት በማይታዘዙት ልጆች ላይ ምን ይመጣል?
5. በቁጥር 7 *"እንግዲህ ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ"* ሲል ከእነማን ጋር እንደ ሆነ እና በምን መልኩ ተካፋይ መሆን እንደሌለባቸው ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የሚከተሉ አማኞች ምን ዐይነት ሕይወት/ምልልስ ሊኖራቸው ይገባል? በዚህ ክፍለ ምንባብ አማኞች ሊያስወግዱ የሚገባቸውን እና ሊከታተሉ የሚገባቸውን ባሕርያት ስንመለከት የእኛስ ሕይወት ምን ይመስላል በማለት ራሳችንን ልንመረምር ይገባል።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለእኛ አሳልፎ የሰጠው በሁሉ አቅጣጫ እግዚአብሔርን የሚያከብር ሕይወት እንድንኖር ነው። በመሆኑም እግዚአብሔርን የምንከተል፣ በፍቅር የምንመላለስ፣ እርሱ የማይከብርባቸውን ነገሮች በሙሉ የምናስወግድ እና እርሱን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት በመኖር በመጨረሻ በማይታዘዙት ልጆች ላይ ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ልንድን ይገባል። አማኞች ከጨለማ ሥራ ጋር ምንም ዐይነት ትብብር የላቸውም። ይልቅስ የክርስቶስ ባሕርይ ተካፋዮች እንደ መሆናቸው የተለየ ሕይወት መኖር ይጠበቅባቸዋል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ"* (ኤፌ. 5÷1)

## ***<u>ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 13</u>***

## ***<u>ዘመኑን ዋጁ፤ ኤፌ. 5÷8-20</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ስንከተል በሕይወታችን ሊታዩ ስለሚገባቸውና ስለማይገባቸው ባሕርያት በዝርዝር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ብርሃን ልጆች በመመላለስ፣ እንደ ጥበበኞች ዘመኑን እንዲዋጁ በኤፌሶን ለነበሩ አማኞች ያስተላለፈውን ምክር እናያለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. ከቁጥር 8 እስከ 10 በማንበብ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች ቀድሞ ምን እንደ ነበሩ እና አሁን እንደ ብርሃን ልጆች እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው በመዘርዘር ተወያዩ።
2. በቁጥር 11 *"ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ ይልቁንም ግለጡት እንጂ"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።
3. ከቁጥር 15 እስከ 17 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ ለነበሩ አማኞች የሰጣቸውን ቢያንስ ሦስት መሠረታዊ ትእዛዞች በመጥቀስ በእያንዳንዱ ላይ ተወያዩ።
4. በቁጥር 18 ላይ *"መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. ከቁጥር 19 እስከ 20 በማንበብ በተሰሎንቄ የነበሩ ቅዱሳን ምን እንዲያደርጉ እንደ ታዘዙ በዝርዝር በማቅረብ ተወያዩ።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- አማኞች የተጠሩት ፍሬ ከሌለው የጨለማ *ሥራ ጋር* እንዲተባበሩ ሳይሆን እንዲገልጡት መሆኑን ተገንዝበን በብርሃን ልንመላለስ ይገባል። በዚህ ክፉ ዘመን የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ በማስተዋል፣ ዘመኑን በጥበብ እየዋጀን በጥንቃቄ መመላለስ ይኖርብናል። ሁለንተናችንን መንፈስ ቅዱስ እንዲቆጣጠር በመፍቀድ በአንደበታችን እና በተግባራችን ሁሉ እግዚአብሔርን እናክብር።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

የጌታ መምጫ በደጅ እንደ መሆኑ መጠን ከምንጊዜውም በላይ ቀኖቹ እየከፉ ስለመሄዳቸው ሁላችንም መመስከር እንችላለን። ቃሉም፣ *"... ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ። ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ"* ይለናል። ስለዚህ ነቅተን እንደ ጥበበኞች ዘመኑን እየዋጀን በጥንቃቄ ልንመላለስ ይገባል። መንፈስ ቅዱስ እንዲቆጣጠረን በመፍቀድም እንደ ብርሃን ልጆች በመንፈስ እንመላለስ።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።"* (ኤፌ. 5÷14-15)

## ***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 14***

## ***አማኝ ባለ ትዳሮች፤ ኤፌ. 5÷21-33***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች እንደ ብርሃን ልጆች እንዲመላለሱና እንደ ጥበበኞች ዘመኑን እንዲዋጁ የሰጣቸውን ምክር ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ባል እና ሚስት (ባለ ትዳሮች) እንደ እግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ አብረው እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን መሠረታዊ መርሆዎች እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 21 *"ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. በቁጥር 22፣ *"ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ"* የሚለው ሐሳብ ምን ማለት እንደ ሆነና በዚህ ዘመን ምን ያህል ተግባራዊ እንደ ሆነ ተወያዩ።
3. ከቁጥር 25 እስከ 28 በማንበብ ለባሎች የተሰጡትን ትእዛዞች በዝርዝር በመጥቀስ ተወያዩ።
4. በዚህ ክፍለ ምንባብ በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙት በጌታና በቤተ ክርስቲያን መካከል ካለው ግንኙነት ጋር እንዴት በንጽጽር እንደ ቀረበ በማሳየት ተወያዩ።
5. በቁጥር 31 *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ"* የሚለው ሐሳብ ስለ ትዳር ምን እንደሚያስተምር በጥልቀት ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ትዳር በእግዚአብሔር የተጀመረ የከበረ ተቋም መሆኑ ይታወቃል። የክርስቲያን ትዳር መሠረቱ ወይም የሚመራው በእግዚአብሔር ቃል ሊሆን ይገባል። በዚህ ዘመን በክርስቲያን ባልና ሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ምን ያህል ባጠናነው ክፍል እንደ ተጻፈው ነው? እንደ አማኞች እግዚአብሔርን በመፍራት፣ እርስ በርስ በመከባበር፣ በመዋደድ፣ ይቅር በመባባል፣ ወዘተ. ትዳራችንን እንደ ቃሉ ልንመራ ይገባል።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እግዚአብሔር በሕይወታችንና በትውልዳችን የሚሠራው በመልካም ትዳር ላይ በተመሠረተ ቤተ ሰብ ውስጥ ነው። በክርስቲያን ትዳር ውስጥ የባል እና የሚስት ድርሻ/ኀላፊነት በቃሉ እንደ ተጻፈው ሊሆን ይገባል። በዚህ ትዳር ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ በተለያዩ ዘመናዊ ሐሳቦች እየተንገዳገደ፣ ብሎም እየፈረሰ ባለበት ዘመን ልንነቃና ትዳራችንን ከጠላት ፍላፃ ልንጠብቅ ይገባል። ለቃሉና ለመንፈሱ ቅድምያ በመስጠት ትዳራችንን ከተለያዩ አደጋዎች እንጠብቅ!

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲሁ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ። "*(ኤፌ. 5÷33)

## ***<u>ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 15</u>***

## ***<u>ክርስቲያናዊ ቤተ ሰብ፣ ሠራተኞችና አሰሪዎች፤ ኤፌ. 6÷1-9</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ ባልና ሚስት (ባለ ትዳሮች) እንደ እግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ አብረው ሊኖሩ የሚያስችላቸውን መሠረታዊ መርሆዎች በኤፌሶን ለነበሩ አማኞች እንደ ሰጠ ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በክርስቲያን ቤተ ሰብ ውስጥ በልጆችና በወላጆች እንዲሁም በክርስቲያን ሠራተኞችና አሰሪዎች መካከል ሊኖር ስለሚገባ ሥነ ምግባር እንመለከታለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. ከቁጥር 1 እስከ 3 በማንበብ ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነት የቀረቡትን መሠረታዊ ነጥቦች በመጥቀስ ተወያዩ። እንደ ተጨማሪ ምሳሌ 1÷8-9 ን አንብቡ።
2. በቁጥር 4፣ *"እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው"* የሚለው ሐሳብ ልጆችን ከመምታት ይልቅ በለዘበ አነጋገር ለመምከር መሞከርና በአግባቡ መገሠጽ ምን ያህል የተሻለ እንደ ሆነ እንደሚያሳይ ተወያዩ።
3. ከቁጥር 5-7 በማንበብ ባሪያዎች/ሠራተኞች ለጌቶቻቸው/ለአሰሪዎቻቸው ማሳየት ስለሚገባቸው ባሕርያት የተነሱትን ነጥቦች በመጥቀስ በእያንዳንዱ ላይ ተነጋገሩ።
4. በቁጥር 8፣ *"ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፥ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።
5. በቁጥር 9 መሠረት ጌቶች/አሰሪዎች ለባሪያዎቻቸው/ለሠራተኞቻቸው ማድረግ ያለባቸው ምንድን ነው?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- ዛሬም ልጆች እንደ ቃሉ ለወላጆቻቸው ሊታዘዙ፣ ወላጆችም ልጆቻቸውን በምክርና በተግሣጽ በአግባቡ ሊያሳድጓቸው ይገባል። ሌላው በሠራተኞችና በአሰሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት እንደ ቃሉ ጤናማ እና እግዚአብሔርን የሚያከብር መሆን አለበት። ለመሆኑ እንደ ክርስቲያን በሥራችን ልናሳያቸው የሚገቡ ባሕርያትን ምን ያህል እያሳየን ይሆን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ለወላጆች መታዘዝ ለልጆች በረከት ነው። ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ስለ ሆኑ ወላጆች ልጆችን በእግዚአብሔር ቃል እየተመራን ልናሳድጋቸው ይገባል። ክርስቲያን በሥራ ቦታው እንደ ቃሉ ታዛዥ፣ ታማኝና ትጉህ ሆኖ ሊያገለግል ይገባዋል። ክርስትናችን እንደ ጨው በገባንበት ሁሉ ያጣፍጥ፤ ብርሃንነታችንም ሳይቋረጥ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ፤ በዚህም የእግዚአብሔር ስም በሁሉ ዘንድ የተወደደና የተመሰገነ ይሁን!

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ።"* (ኤፌ. 6÷6)

## ***ወደ ኤፌሶን ሰዎች ጥናት 16***

## ***መንፈሳዊ ውጊያ፤ ኤፌ. 6÷10-24***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት በክርስቲያን ቤተ ሰብ ውስጥ በልጆችና በወላጆች እንዲሁም በክርስቲያን ሠራተኞችና አሰሪዎች መካከል ሊኖር ስለሚገባ ሥነ ምግባር ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ክርስቲያኖች መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር ሳይሆን ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፣ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር፣ በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር በመሆኑ መንፈሳዊ ትጥቅ መታጠቅና በጌታና በኀይሉ ችሎት በርትቶ መዋጋት እንደሚገባ እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ከቁጥር 10 እስከ 12 በማንበብ የአማኞች ጠላት ማን እንደ ሆነ እና በእነዚህ ቁጥሮች በምን መልኩ እንደ ተገለጸ ተወያዩ።
2. ከቁጥር 10 እስከ 13 ላይ በተጻፈው መሠረት በጌታና በኀይሉ ችሎት እንበረታ ዘንድ፣ እንዲሁም በክፉ ቀን ለመቃወምና ሁሉንም ፈጽመን ለመቆም ምን እንድናደርግ ታዘናል?
3. ከቁጥር 14 እስከ 17 መሠረት የአማኞች የጦር ዕቃዎች ምን ምን እንደ ሆኑ በመዘርዘር እያንዳንዱን በስፋት ተወያዩ።
4. በቁጥር 18 ላይ በተጻፈው ሐሳብ መሠረት አማኞች እንዴትና ስለ ማን ሊጸልዩ ይገባል?
5. በቁጥር 19 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ምን እንዲጸልዩለት ጥያቄ አቀረበ?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- የዲያብሎስን ሽንገላ እንቃወም ዘንድ፣ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር እንጋደል ዘንድ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ እናንሳ። እውነትን ታጥቀን፣ ጽድቅን ለብሰን፣ የመንፈስን ሰይፍ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ይዘን መንፈሳዊ ውጊያ እናድርግ። አማኝ ሁል ጊዜም በመንፈሳዊ ውጊያ ላይ ነው!
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ክርስቲያኖች መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር ሳይሆን ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር መሆኑን ተረድተን፣ መንፈሳዊ ትጥቅ ታጥቀን መንፈሳዊ ውጊያ ስናደርግ በጌታና በኀይሉ ችሎት ስለምንበረታ ድሉ የኛ ነው። በተጨማሪም ስለ ራሳችንም ሆነ ስለ ሌሎች ዘወትር በመንፈስ መጸለይ ይጠበቅብናል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።"* (ኤፌ. 6÷10)

## መጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

**መግቢያ**

1ኛ ተሰሎንቄ ከቀደምት የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች መካከል አንዱ እንደ ሆነ ይነገራል። እንደውም አንዳንድ ምሁራን እንደሚናገሩት ከሆነ ይህ ደብዳቤ ከወንጌላትና ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ቀድሞ የተጻፈ ሊሆን ይችላል። ይህን ደብዳቤ በማንበብ በይዘቱ ላይ ውይይት ከማድረጋችን በፊት የደብዳቤውን ታሪካዊ ዳራ እንደሚከተለው በአጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን።

**ጸሐፊ**፤ የ1ኛ ተሰሎንቄ ጸሐፊ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መሆኑ በመልእክቱ የመክፈቻ ቁጥር ላይ በግልጽ ተጽፏል፤ *"ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም"* (1÷1) ይላል። ስልዋኖስ/ስሉያኖስ ወይም ሲላስ እና ጢሞቴዎስ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር አብሮ ሠራተኞች መሆናቸውንና ከመልእክቱ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማሙ መሆናቸውን ለመግለጽ ስማቸው ቢጠቀስም የመልእክቱ ጸሐፊ በመጀመሪያ ላይ የተቀመጠው ጳውሎስ ነው። እንደ ተጨማሪ ማስረጃ 2÷18 እና 5÷27 ን መመልከት ይቻላል። ሌላው የቤተ ክርስቲያን አባቶችም (ለምሳሌ፤ የእስክንድርያው ክሌመንት፣ ተርቱሊያን እና ኢሬኔዎስ) ደብዳቤው በጳውሎስ መጻፉን መስክረዋል።

**ተቀባይ**፤ የ1ኛ ተሰሎንቄ ደብዳቤ ተቀባይ በተሰሎንቄ የነበረች ቤተ ክርስቲያን መሆኑ በመግቢያው ላይ ተጽፏል፤ *"በእግዚአብሔር አብ፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን"* (1÷1) ይላል። ተሰሎንቄ የሮማውያን ግዛት የነበረችው የመቄዶንያ ትልቋ እና ዋና ከተማ ነበረች። ከሮም ወደ ምሥራቃዊ አውራጃዎች በሚወስደው ዋና መንገድ በኤግናቲያን መንገድ ላይ ትገኛለች። ከተማዋ የንግድ ማዕከል ሆና አገልግላለች። ዛሬ ቴሳሎኒኪ (Thessaloniki) ወይም ሳሎኒካ (Salonica) በመባል ትታወቃለች። የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት በሐዋርያት ሥራ ምእራፍ 17 ላይ ተመዝግቦ ይገኛል። ይህ ምእራፍ እንደሚነግረን ጳውሎስና ወዳጆቹ (ሲላስና ጢሞቴዎስ) በሁለተኛው ሚስዮናዊ ጉዞ ከፊልጵስዩስ ተነስተው በአምፊጶልስ እና በአጶሎንያ በኩል አልፈው ተሰሎንቄ ደረሱ፤ ጳውሎስ እንደ ልማዱ ወዲያውኑ ምኵራብን አግኝቶ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ሰንበትን ከአይሁድ ጋር ተነጋገረ፤ ከእነርሱም አንዳንዶቹ ተረድተው ከሚያመልኩም ከግሪክ ሰዎች ብዙ፣ ከከበሩትም ሴቶች ጥቂቶች ያይደሉ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ተባበሩ፤ አይሁድ ግን ቀንተው ከሥራ ፈቶች ክፉ ሰዎችን በማምጣት ሕዝብንም ሰብስበው ከተማውን አወኩ፤ ወዲያውም ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው።

**የተጻፈበት ጊዜና ቦታ**፤ በሐዋርያት ሥራ 17 ላይ የሚገኘውን ታሪክ እና የ1ኛ ተሰሎንቄን ይዘት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ በሁለተኛው ሚስዮናዊ ጉዞ ላይ በነበረበት ጊዜ በ51/52 ዓ.ም አካባቢ ከቆሮንቶስ እንደ ጻፈ ይታመናል።

**የመልእክቱ ዐላማ**፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተጀመረች በኋላ ከተሰሎንቄ በድንገት መውጣቱ የወንድሞች ሁኔታ እንዲያሳስበው ያደረገ ይመስላል። ጢሞቴዎስ በአቴና ከጳውሎስ ጋር በተገናኘበት ጊዜ (የሐዋ. 17÷14-16) አዳዲሶቹን ደቀ መዛሙርት በእምነት ለማበረታታት እና በስደት እንዴት እየጸኑ መሆናቸውን ለማወቅ ወዲያውኑ ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ እንዲልክ አነሳስቶታል (1ኛ ተሰ. 3÷1-5)። ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር ወደ ቆሮንቶስ ሲመለስ (የሐዋ. 18÷5) ዜናው በአብዛኛው የሚያበረታታ ነበር (1ኛ ተሰ. 3÷6-7)። ከባድ ስደት ቢኖርም በጥንካሬ ጸንተዋል (1ኛ ተሰ. 2÷13-16) ለሌሎችም ዐርዓያ መሆናቸውን አስመስክረዋል (1ኛ ተሰ. 1÷6-8)። ሆኖም፣ እንደ ማንኛውም አዳጊ ቤተ ክርስቲያን፣ በቅድሰና ስለ መኖር ተጨማሪ ትምህርት (1ኛ ተሰ. 4÷1-12)፣ እንዲሁም በክርስቶስ አምነው ስለ ሞቱ ቅዱሳን ከጌታችን መምጣት ጋር በተያያዘ የማጽናኛ መልእክት (1ኛ ተሰ. 4÷13-18) ያስፈልጋቸው ነበር። የዚህ ደብዳቤ እያንዳንዱ ምእራፍ የሚያበቃው የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በመጥቀስ መሆኑ ልዩ ነው (1ኛ ተሰ. 1÷10፤ 2÷19፤ 3÷13፤ 4÷13-18፤ 5÷23)። ይህም የመልእክቱ ጭብጥ በጽናት እና በቅድስና አኗኗር ላይ አጽንኦት በመስጠት የጌታን ዳግም ምጽአት በትጋት እንዲጠባበቁ ማሳሰብ እንደ ሆነ ይጠቁማል።

## ***<u>ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 1</u>***

## ***<u>እግዚአብሔርን የሚያስመሰግን ሕይወት፤ 1ኛ ተሰ. 1÷1-4</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

የ1ኛ ተሰሎንቄ መልእክት የመጀመሪያ የጥናት ክፍል በሆነው በዛሬው ጥናታችን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሌሎቹ ደብዳቤዎቹ እንደሚያደርገው በመግቢያ ሰላምታ እንዴት እንደ ጀመረ እንመለከታለን። በተለይም ከሰላምታው ጋር በተያያዘ መልኩ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች ከተቀበሉት ወንጌል የተነሳ እያሳዩ ስላሉት የእምነት ሥራ፣ ስለ ፍቅራቸው ድካም እና በተስፋ ስለ መጽናታቸው እግዚአብሔርን እንዴት እንዳመሰገነ እንወያያለን።

*<u>የመዋያያ ጥያቄዎች</u>*

1. በቁጥር 1 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በሰላምታው ስለ ስልዋኖስ እና ስለ ጢሞቴዎስ መግለጽ ለምን አስፈለገው? (ከየሐዋርያት ሥራ 17÷1-4 እና ከ1ኛ ተሰሎንቄ 3÷2 ጋር በማዛመድ ተወያዩ።
2. በቁጥር 1፣ *"... በእግዚአብሔር አብ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደምትሆን"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ከቁጥር 2 እስከ 3 በማንበብ ጳውሎስና ወዳጆቹ በጸሎታቸው ጊዜ በተሰሎንቄ ስለ ነበሩ አማኞች ሲያስቡ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ያደረጉአቸው ሦስት መሠረታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?
4. ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆች በተሰሎንቄ ስለ ነበሩ አማኞች ሁል ጊዜ የሚያስቡ፣ በእነርሱ ምክንያት እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ መሆናቸው ምን ያስተምረናል? በዚህ ዘመን አገልጋዮች ስለሚያገለግሉት ሕዝብ ምን ያህል ያስባሉ/ይጸልያሉ?
5. በቁጥር 4፣ *"በእግዚአብሔር የምትወደዱ ወንድሞች ሆይ እንደ ተመረጣችሁ አውቀናልና"* ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- በተሰሎንቄ እንደ ነበሩ አማኞች ዛሬም የእምነት ሥራ፣ ፍቅር እና በተስፋ መጽናት የአማኞች መገለጫ ባሕርያት ሊሆኑ ይገባል። እነዚህ ባሕርያት ምን ያህል መታወቂያችን ወይም መገለጫችን እንደ ሆነ ራሳችንን እንመርምር። ለመሆኑ ሰዎች እኛን ሲያስቡ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ይሆን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ ስለ ነበሩ አማኞች ሲያስብ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ያደረጉት ክርስቲያናዊ ባሕርያት የእኛም መገለጫ ሊሆኑ ይገባል። እንደ አማኞች በሥራ በተገለጠ እምነት፣ ግብዝነት በሌለበት ፍቅር እና በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ተስፋ በመጽናት ልንመላለስ ይገባል።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"በጸሎታችን ጊዜ ስለ እናንተ ስናሳስብ፥ የእምነታችሁን ሥራ የፍቅራችሁንም ድካም በጌታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን የተስፋችሁን መጽናት በአምላካችንና በአባታችን ፊት ሳናቋርጥ እያሰብን፥ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን።"* (1ኛ ተሰ. 1÷3)

## ***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 2***

## ***በምሳሌነት መመላለስ፤ 1ኛ ተሰ. 1÷5-10***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ ለነበሩ አማኞች ያቀረበውን ሰላምታ በተለይም ሰምተው ከተቀበሉት ወንጌል የተነሳ እያሳዩ ስላሉት ክርስቲያናዊ ባሕርያት እግዚአብሔርን እንዴት እንዳመሰገነ ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች በሕይወት ምልልሳቸው ለሌሎች ምሳሌ መሆናቸውንና ይህም ደግሞ በዙሪያቸው ባሉት ዘንድ መልካም ተጽእኖ ማምጣቱን እንደ መሰከረላቸው እንመለከታለን።

*የመዋያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 5 መሠረት ወንጌል ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የደረሰው በምን ዐይነት ሁኔታ ነበር? ይህስ ስለ ወንጌል ምን ያስተምራል?
2. በቁጥር 6 መሠረት የተሰሎንቄ ሰዎች ወንጌልን የተቀበሉት እንዴት ነበር? ሌላው፣ *"እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ"* ሲላቸው ምን ማለቱ ነው?
3. በቁጥር 7 መሠረት በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች ሕይወት/ባሕርይ በመቄዶንያና በአካይያ ባሉት ምእመናን ላይ ምን ዐይነት ተጽእኖ እንዳመጣ ተወያዩ።
4. በቁጥር 8 መሠረት የተሰሎንቄ ሰዎች የጌታ ቃል በስፍራ ሁሉ እንዲሰማ ያደረጉት በምን መንገድ ነበር?
5. ቁጥር 9 እና 10 ን በማንበብ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች የእምነት ምሳሌ እንዲሆኑና በሌሎች ላይ በጎ ተጽእኖ እንዲያሳድሩ ያደረገው የእምነት ሥራቸው ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ልክ እንደ ተሰሎንቄ ሰዎች ዛሬም አማኞች ምሳሌያዊ የሆነ ሕይወት በመኖር በዙሪያቸው ባሉት ሰዎች ላይ አዎንታዊ/በጎ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይገባል። ለመሆኑ ለሌሎች ምሳሌ የሆነ ሕይወት አለን? በዙሪያችን ባሉት ሰዎች ዘንድስ የምንታወቀው በምን ይሆን? እንግዲህ ምሳሌ ባልሆንበት አቅጣጫ ራሳችንን በመመርመር አካሄዳችንን እናስተካክል። ሌላው ወንጌል በቃል ብቻ ወደ እኛ እንዳልመጣ እናስተውል!
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

አማኞች ሌሎችን ወደ ክርስቶስ የሚመራ ሕይወት ሊኖሩ ይገባል። ምሳሌ የሆነ ወይም በጎ ተጽእኖ የሚያመጣ ሕይወት ቤተ ሰቦቻችን፣ ጓደኞቻችን፣ የሥራ ባልደረቦቻችን እና የምንኖርበት ማኅበረ ሰብ ወደ ክርስቶስ ይመራል። ሌላው ወንጌል ወደ እኛ የመጣው በቃል ብቻ ሳይሆን በኀይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንደ ሆነ አንዘንጋ!

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ስለዚህም በመቄዶንያና በአካይያ ላሉት ምእመናን ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁላቸው።"* (1ኛ ተሰ. 1÷7)

## ***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 3***

## ***የሐዋርያው ጳውሎስ የወንጌል ተጋድሎ፤ 1ኛ ተሰ. 2÷1-12***

### ***መግቢያ***

ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች በሕይወት ምልልሳቸው ለሌሎች ምሳሌ መሆናቸውን እና በዙሪያቸው ባሉት ላይም መልካም ተጽእኖ ማምጣታቸውን እንደ መሰከረ ባለፈው ጥናት ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ወንጌል በብዙ መከራና ተጋድሎ ለተሰሎንቄ ሰዎች እንዴት እንዳደረሰላቸው እንመለከታለን።

*የመዋያያ ጥያቄዎች*

1. ከቁጥር 1 እስከ 4 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆቹ ወንጌልን በምን መልኩ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች እንዳደረሱ ተወያዩ።
2. ቁጥር 5 እና 6 ን በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆች፣ *"... አልተናገርንም ... አልሠራንም ... አልፈለግንም"* በማለት ስለ ወንጌል የነበራቸውን ንጹሕ የልብ መነሳሳት እንዴት እንዳቀረቡ ተወያዩ?
3. በቁጥር 6፣ *"የክርስቶስም ሐዋርያት እንደ መሆናችን ልንከብድባችሁ ስንችል ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም"* ሲል ምን ማለቱ ነው? (ከ1ኛ ቆሮ. 9÷7-12 ጋር በማዛመድ አብራሩ)።
4. በቁጥር 7 እና 8 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የነበረውን ፍቅር፣ በምን መልኩ እንዳገለገሏቸው ለመግለጽ የተጠቀመውን ምሳሌና ገለጻ በመጥቀስ ተወያዩ።
5. ከቁጥር 9 እስከ 12 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆች የተሰሎንቄን ሰዎች በምን መልኩ እንዳገለገሉና ይህን ዋጋ በመክፈል ያገለገሉበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆች የተሰሎንቄን ሰዎች ለማገልገል የከፈሉት ዋጋ፣ ስለ አገልግሎት ያላቸው ግንዛቤ ራሳችንን እንድንመረምር ሊያደርገን ይገባል። ዛሬ ዋጋ ከፍለን ለማገልገል ምን ያህል ዝግጁ ነን? ጌታን ስናገለግልስ ውስጣዊው ፍላጎታችን ("ሞቲቫችን") ምን ያህል ጤናማ ነው? የምናገለግለው ለሌሎች ጥቅም ወይስ ለምናተርፈው ምድራዊ የግል ክብርና ጥቅም?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ይህ ክፍለ ምንባብ በየትኛውም መንገድ ጌታን ስናገለግል ብድራታችንን ከራሱ ከጌታ ብቻ እየጠበቅን ለእኛ ሳይሆን ለእርሱ ክብር በንጹሕ ሕሊና፣ በቅን ልብ፣ በፍቅር፣ በትጋት እና አገልግሎት የሚያስከፍለውን ዋጋ በመክፈል ልናገለግል እንደሚገባ በማሳየት ይሞግታል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና።"* (1ኛ ተሰ. 2÷8)

## ***<u>ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 4</u>***

## ***<u>ቃሉን እንደ እግዚአብሔር ቃል መቀበል፤ 1ኛ ተሰ. 2÷13-20</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን በብዙ በመከራና ተጋድሎ ለተሰሎንቄ ሰዎች እንዳደረሰና በጤናማ “ሞቲቭ” እንዴት እንዳገለገላቸው ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የተሰሎንቄ አማኞች የሐዋርያው ጳውሎስን መልእክት እንደ ሰው ቃል ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዴት እንደ ተቀበሉ እና ጳውሎስ ስለ እነርሱ እግዚአብሔርን በምን መልኩ እንዳመሰገነ እንመለከታለን።

*<u>የመዋያያ ጥያቄዎች</u>*

1. በቁጥር 13፣ *“… እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት …”* ሲል ምን ማለቱ ነው? እንደ ሰው እና እንደ እግዚአብሔር ቃል የመቀበል ልዩነቱስ ምንድን ነው?
2. ከቁጥር 14 እስከ 16 በማንበብ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች በይሁዳ ካሉት ጋር የሚመሳሰሉት በምን እንደ ሆነ ግለጹ።
3. በቁጥር 17 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆቹ የተሰሎንቄን ሰዎች ለማየት ያላቸው ናፍቆት ስለ አገልግሎት ምን ያስተምራል? አገልጋይ ለሚያገለግለው ሕዝብ ምን ዐይነት ልብ ሊኖረው ይገባል?
4. ቁጥር 18፣ *“ወደ እናንተ ልንመጣ ወደን ነበርና፥ እኔ ጳውሎስም አንድና ሁለት ጊዜ፥ ሰይጣን ግን አዘገየን”* ይላል፤ ለመሆኑ ሰይጣን የማዘግየት ሥልጣን አለው? ለምንስ አዘገያቸው? ይህ ሐሳብ ስለ መንፈሳው ውጊያ ምን ያስተምራል?
5. ከቁጥር 19 እስከ 20 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ጌታ ኢየሱስ በክብር ሲመጣ *“እናንተ ደግሞ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና”* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- ቃሉን እንደ ሰው ቃል ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል መቀበል በሕይወታችን ላይ የሚታይ ለውጥ ያመጣል። ለመሆኑ ከተቀበልነው ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ በሕይወታችን ላይ ምን ዐይነት ለውጥ መጥቷል? አኗኗራችንስ ቀድሞ ከነበረው ከአሮጌው ሕይወት በምን መልኩ የተለየ ነው?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

የምናነበውን እና እንደ ቃሉ በትክክል የሚያገለግሉ ሰዎች የሚናገሩትን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰው ቃል ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል በመውሰድ ልንታዘዝ ይገባል። ቃሉን በአክብሮት የሚቀበሉ እና በመታዘዝ ተግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎች የተለወጠ ሕይወት ይኖራቸዋል። ሌላው አገልጋይ ለሚያገለግለው ሕዝብ ፍቅር እና ልዩ አክብሮት ሊኖረው ይገባል።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*“ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን።”* (1ኛ ተሰ. 2÷13)

## ***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 5***

## ***በመከራ መጽናት፤ 1ኛ ተሰ. 3÷1-5***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት የተሰሎንቄ አማኞች ሐዋርያው ጳውሎስ ያመጣላቸውን መልእክት እንደ ሰው ቃል ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል ተቀብለው በሕይወታቸው ክርስቶስን በመግለጣቸው እነ ጳውሎስ ስለ እነርሱ ሳያቋርጡ እግዚአብሔርን እንዳመሰግኑ ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች በመከራ እንዳይናጉና በእምነታቸው እንዲጸኑ ይመክራቸው ዘንድ ከእርሱ ጋር የክርስቶስ ወንጌል አብሮ ሠራተኛ የሆነውን ጢሞቴዎስን እንደ ላከላቸው እንመለከታለን።

*የመዋያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 1 እና 5 መሠረት እነ ጳውሎስ ይታገሡ ዘንድ ያልተቻላቸውና በአቴና ብቻቸውን ሊቀሩ የፈቀዱበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
2. በቁጥር 2 ገለጻ መሠረት ጢሞቴዎስ ምን ዐይነት አገልጋይ ነበር? ወደ ተሰሎንቄስ የተላከው ለምን ዐላማ ነበር?
3. በቁጥር 3 እና 4 ሐዋርያው ጳውሎስ በመከራ እንዳይናወጡ ሲመክራቸው፣ *"ለዚህ እንደ ተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. አገልግሎት እና መከራ መቀበል በምን ይገናኛሉ? መከራ የማይመለከተው/የማይነካው አገልግሎትስ አለ?
5. በቁጥር 5 ሐዋርያው ጳውሎስ *"ፈታኝ"* ብሎ የገለጠው ማንን ይመስላችኋል?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል! ስለ ወንጌል በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ልናልፍ እንችላለን። በዚህ ዘመን እምነታችንን ለማናጋት እና አገልግሎታችንን ለማበላሸት ሊገጥሙን ከሚችሉ ልዩ ልዩ ፈተናዎች መካከል ጥቂቶቹን በመጥቀስ የመውጫ መንገዶቹንም አብራችሁ ጠቁሙ።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመውያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

በዚህ በወደቀ ዓለም ውስጥ እስካለን ድረስ እንደ ግልም ሆነ እንደ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ መከራ ወይም ፈተና ሊገጥመን ይችላል። የመከራ ምንጩ ደግሞ ልዩ ልዩ እንደ ሆነም ይታወቃል። በተለይም እንደ ቃሉ እየኖርን ስለ ወንጌል የሚደርስብንን መከራ በጌታ ጸጋ በመበርታትና በጽናት በመቆም እስከ መጨረሻው መዝለቅ ይጠበቅብናል። በቃል እየበረታን፣ በጸሎት ከጌታ ጋር እየተጣበቅን፣ በጸጋው እየተደገፍን፣ ሥጋችንን እየጎሸምን እና ሰይጣንን አጥብቀን እየተቃወምን ሳንናወጥ እስከ መጨረሻው በእምነት ልንጸና ይገባል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"በዚህ መከራ ማንም እንዳይናውጥ፥ ለዚህ እንደ ተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና።"* (1ኛ ተሰ. 3÷3)

## ***<u>ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 6</u>***

## ***<u>በመጽናት መጽናናት፤ 1ኛ ተሰ. 3÷6-13</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች በመከራ እንዳይናጉና በእምነታቸው እንዲጸኑ ይመክራቸው ዘንድ ከእርሱ ጋር የክርስቶስ ወንጌል አብሮ ሠራተኛ የሆነውን ጢሞቴዎስን እንደ ላከላቸው ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጢሞቴዎስ ከተላከበት ይዞት በተመለሰው የተሰሎንቄ አማኞች ፍቅርና የእምነት ጽናት ዜና ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆቹ መጽናናታቸውን እናያለን።

*<u>የመዋያያ ጥያቄዎች</u>*

1. ከቁጥር 6 እስከ 8 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስን *"በችግራችንና በመከራችን ሁሉ ስለ እናንተ ተጽናናን"* እንዲል ያደረገው፣ ጢሞቴዎስ በተሰሎንቄ ስለ ነበሩ አማኞች ሕይወት ይዞት የተመለሰው የምስራች ምን ምን እንደ ሆኑ በመዘርዘር ተወያዩ።
2. በቁጥር 9 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *"ፊታችሁን ልናይ በእምነታችሁም የጎደለውን ልንሞላበት ..."* ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆቹ ሌሊትና ቀን ከመጠን ይልቅ የሚጸልዩ መሆናቸው፣ በተሰሎንቄ ሰዎች መደሰታቸውና በእነርሱ ምክንያት እግዚአብሔርን ማመስገናቸው ስለ አገልጋይና አገልግሎት ምን ሊያስተምር ይችላል? (ቁጥር 9-10)
4. በቁጥር 11 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጸው እንዴት ነው?
5. በቁጥር 12 እና 13 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ ለነበሩ አማኞች እግዚአብሔር እንዲያበዛላቸውና እንዲጨምርላቸው የጸለየው ምንን እንደ ሆነ ተወያዩ።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- የዛሬ ክፍል አገልጋይ ለሚያገለግለው ሕዝብ ምን ዐይነት መጋቢያዊ ልብና ፍቅር ሊኖረው እንደሚገባ ያሳያል። የአማኞች በመከራ መጽናትና በፍቅር ማደግ አገልጋዮቻቸውን ደስ ሊያሰኝ ይገባል። ሕይወታችን ምን ያህል አገልጋዮችን ደስ በማሰኘት ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዲያመጡ ያደርግ ይሆን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር በቶሎ ይመጣል! እንግዲህ እርሱ እስኪመጣ ድረስ በቅድስና እና ነቀፋ በሌለበት ሕይወት በመኖር ልባችን ይጽና። እንደ አገልጋዮችም ብዙዎችን ለዚህች ቀን በማዘጋጀት ሥራ ወይም አገልግሎት ልንተጋ ይገባል። በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር እርስ በእርሳችን ያለንን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችንን ያብዛ፤ ይጨምርም!

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በእምነታችሁ በኩል በችግራችንና በመከራችን ሁሉ ስለ እናንተ ተጽናናን"* (1ኛ ተሰ. 3÷7)

## ***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 7***

## ***በቅድስና መመላለስ፤ 1ኛ ተሰ. 4÷1-8***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ጢሞቴዎስ ከተላከበት ይዞት በተመለሰው የተሰሎንቄ አማኞች ፍቅርና የእምነት ጽናት ዜና ሐዋርያው ጳውሎስና ወዳጆቹ መጽናናታቸውን አይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ይችሉ ዘንድ እንዴት በቅድስና መኖር እንደሚገባቸው ለተሰሎንቄ ሰዎች የሰጠውን ምክር እንመለከታለን።

### ***የመዋያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 1 ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞችን በጌታ በኢየሱስ የሚለምናቸውና የሚመክራቸው ምን እንዲያደርጉ/እንዲሆኑ ነው?
2. በቁጥር 2 እና 3 መሠረት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የእግዚአብሔር ትእዛዝና ፈቃድ ተብሎ የተጠቀሰው ምንድን ነው?
3. በቁጥር 4 እና 5 መሠረት አንድ አማኝ የራሱን ዕቃ /የገዛ ሰውነቱን/ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ ከምን መራቅ አለበት?
4. በቁጥር 6 እና 7 መሠረት፣ *“ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል”* ያለው በምንድን ነው? ይህን ማድረግ የሚያስከትለው የጌታ ፍርድስ ምንድን ነው?
5. በቁጥር 8፣ *“እንግዲህ የሚጥል ሰውን የጣለ አይደለም መንፈስ ቅዱስን በእናንተ እንዲኖር የሰጠውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ”* ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- የእግዚአብሔር ፈቃድ መቀደሳችን ነው! ይህንን በመረዳት እግዚአብሔር ከማይከብርባቸው ነገሮች ሁሉ በመራቅ በቅድስና መኖር ይጠበቅብናል። ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናል! እንግዲህ ከርኩሰት በመለየት የገዛ ሰውነታችን በክብር እንዲገኝ እንጠብቀው።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እግዚአብሔር ለርኵሰት ሳይሆን ለቅድስና ስለ ጠራን ሁለንተናችን ማለትም አንደበታችን፣ ዐይናችን እና ሌሎችም የአካል ክፍሎቻችን የጌታ እንደ ሆኑ አውቀን በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ በውጭ፣ በቃልም ሆነ በሥራ በቅድስና በመመላለስ እግዚአብሔርን ደስ ልናሰኘው ይገባል። ጌታ ይርዳን!

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*“ለርኵሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናልና።”* (1ኛ ተሰ. 4÷7)

## ***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 8***

## ***የእርስ በርስ ፍቅርና የሥራ ትጋት፤ 1ኛ ተሰ. 4÷9-12***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት የተሰሎንቄ ሰዎች እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንዴት በቅድስና መኖር እንደሚገባቸው ሐዋርያው ጳውሎስ የሰጣቸውን ምክር ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የተሰሎንቄ አማኞች እርስ በርሳቸው ባላቸው የወንድማማች ፍቅር፣ በሰላምና እና በሥራ ትጋት በውጭ ባሉት ዘንድ ጌታን እያስከበሩ እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸው የተሰጣቸውን መልእክት እንቃኛለን።

### ***የመዋያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 9፣ *"እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. የተሰሎንቄ ሰዎች በመቄዶንያ ሁሉ ላሉት ወንድሞች ያደረጉት ምንድን ነው?
3. ከቁጥር 10 እስከ 12 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች እንዲያደርጉ ያበረታታቸው ምን ምን እንደ ሆኑ ጥቀሱ።
4. ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *"ከፊት ይልቅ ልትበዙ፣ በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ ልትቀኑ የራሳችሁንም ጉዳይ ልትጠነቀቁ"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።
5. አማኞች በሥራ ተግተው ራሳቸውን መቻላቸው እና የሌላ ሰው ሸክም አለመሆናቸው በውጭ ባሉ ሰዎች ዘንድ ምን ዐይነት ምስክርነት እንዲኖራቸው ያደርጋል?

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- አማኞች እርስ በርሳቸው ባላቸው ግንኙነት፣ በተገለጠ ፍቅራቸው እና የሚያስፈልጋቸውን ለማግኘት በትጋት መሥራታቸው በውጭ ያሉትን ሰዎች (እስከ አሁን ያላመኑትን) ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊያመጣ ይችላል። በአንጻሩ ደግሞ የትኛውም ከተጠቀሱት መገለጫዎች የጎደለ ሕይወት ለብዙዎች እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ምሳሌ የሆነ ሕይወት በመኖር ለብዙዎች መዳን መንገድ/ምክንያት እንሁን!
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እኛም በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ በየትኛውም ስፍራ በወንድማማች ፍቅር እርስ በርስ በመዋደድ፣ ሰላማውያን በመሆን፣ በሥራ በመትጋት እና በጥንቃቄ በመኖር/በመመላለስ በውጭ ላሉት ወንድሞችና እኅቶች ጌታን ልናሳይና ልክናስከብረው ይገባል። ጌታ ይርዳን!

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"በውጭ ባሉት ዘንድ በአገባብ እንድትመላለሱ፥ አንዳችም እንዳያስፈልጋችሁ በእጃችሁ ልትሠሩ እንለምናችኋለን።"* (1ኛ ተሰ. 4÷12)

## ***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 9***

## ***ተስፋ እንደ ሌላቸው እንዳታዝኑ፤ 1ኛ ተሰ. 4÷13-18***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት የተሰሎንቄ አማኞች በእርስ በርስ የወንድማማች ፍቅር፣ በሰላምና እና በሥራ ትጋት በውጭ ባሉት ዘንድ ጌታን እያስከበሩ እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸው ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተላለፈላቸውን መልእክት ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የተሰሎንቄ አማኞች አንቀላፍተው ስላሉቱ/በሞት ስለተለዩዋቸው አማኞች/ ተስፋ እንደ ሌላቸው እንደ ሌሎች ሰዎች/ኢ-አማንያን/ እንዳያዝኑ ሐዋርያው ጳውሎስ የሰጣቸውን መልእክት እንቃኛለን።

### ***የመዋያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 13 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች አንቀላፍተው ስላሉት ሰዎች ምን እንዳያደርጉ እንደሚወድ ይናገራል? ምንስ እንዲያውቁ ይወዳል?
2. በቁጥር 14 መሠረት በኢየሱስ አምነው ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?
3. ከቁጥር 15 እስከ 17 እንደሚናገረው ከሆነ ሕያዋን የሆኑት ጌታን በአየር ለመቀበል ሲነጠቁ በጌታ አምነው ያንቀላፉ ምን ይሆናሉ?
4. *"ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።
5. በዚህ ክፍለ ምንባብ መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ የሚሆኑ ዋና ዋና ክንውኖች ምን ምን እንደ ሆኑ በዝርዝር በማቅረብ ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ይመጣል! እርሱ ዳግም ሲመጣ በእርሱ አምነው ያንቀላፉት ይነሣሉ፤ ሕያዋንም የሆኑ (በሕይወት ያሉ) እርሱን በአየር ለመቀበል ይነጠቃሉ። በመሆኑም በጌታ ስላንቀላፉት ሰዎች ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች ልናዝን አይገባም። ሌላው የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በየዕለቱ እናስብ!
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ተስፋችን የሆነው ጌታ በመላእክት ታጅቦ በክብር የሚመለስበት ጊዜ እየቀረበ ነው። የኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ ለሚያምኑ ሁሉ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ ትንሣኤ ወይም ንጥቀት ይሆንላቸዋል። እኛ አማኞች ይህ ተስፋ ስላለን ሞትን ስናስብ ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች ልናዝን አይገባም። ይልቅስ እርስ በርሳችን በዚህ ቃል እየተጽናናን ጌታን በትዕግስት ልንጠባበቀው ይገባል። ማራናታ! አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና!!!

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፣ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።"*(1ኛ ተሰ. 4÷14)

## ***<u>ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 10</u>***

## ***<u>እንግዲያስ እንንቃ፤ 1ኛ ተሰ. 5÷1-11</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት የተሰሎንቄ አማኞች አንቀላፍተው ስላሉቱ ወይም በሞት ስለተለዩዋቸው አማኞች ተስፋ እንደ ሌላቸው እንደ ሌሎች ሰዎች/ኢ-አማንያን/ እንዳያዝኑ ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተላለፈላቸውን መልእክት ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የተሰሎንቄ አማኞች እንደ ብርሃን ልጆች ነቅተው በመጠን እንዲኖሩ ሐዋርያው ጳውሎስ የሰጣቸውን መልእክት እንዳስሳለን።

### ***<u>የመዋያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 1 እና 2 ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ስለ ዘመናትና ስለ ወራት *"ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም"* ያለው ለምንድን ነው?
2. በቁጥር 3፣ *"ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም"*የተባሉት ምን ዐይነት ሰዎች ናቸው?
3. በቁጥር 4 እና 5 መሠረት የተሰሎንቄ ሰዎች ቀኑ እንደ ሌባ የማይደርስባቸው ምን ዐይነት ሰዎች ስለ ሆኑ ነው? "የብርሃን ልጆች" እና "የቀን ልጆች" መገለጫ ልዩነታቸው ምን ይመስላችኋል?
4. ከቁጥር 6 እስከ 8 በማንበብ ስለ መንቃትና በመጠን ስለ መኖር ተግባራዊ መገለጫዎች የሆኑ ነጥቦችን በመዘርዘር ተወያዩ።
5. በቁጥር 9 እና 10 መሠረት እግዚአብሔር ሰዎችን ለቍጣ ላለመምረጡ ማሳያው ምንድር ነው?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- በክርስቶስ ያመንን ሁሉ በጨለማ አይደለንም፤ የብርሃን ልጆች፣ የቀንም ልጆች ነን። እንግዲህ ከቀን ስለ ሆንን የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን ልንኖር ይገባል። ለመሆኑ በመንፈሳዊ ሕይወታችን በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ምን ያህል እንደ ብርሃን ልጆች እየተመላለስን ይሆን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከማመናችን የተነሣ ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ወጥተን የብርሃን ልጆች ሆነናል። እንግዲህ እንደ ቀን ልጆች በፍቅራችን እየተገለጥን፣ የዘላለምን መዳን ተስፋ ተላብሰን እና ነቅተን በመጠን እንኑር። እግዚአብሔር የመረጠን ለቁጣ ሳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ።"* (1ኛ ተሰ. 5÷6)

## ***<u>ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 11</u>***

## ***<u>ለመሪዎችና ለሕዝቡ የተሰጠ ኀላፊነት፤ 1ኛ ተሰ. 5÷12-18</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች እንደ ብርሃን ልጆች ነቅተው በመጠን እንዲኖሩ የሰጣቸውን መልእክት ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሕዝቡን ለመምራት በእግዚአብሔር የተሾሙ አገልጋዮችን ኀላፊነት እና የሕዝቡን ድርሻ እንዲሁም ሁለቱም ወገኖች በጋራ ያላቸውን ኀላፊነት/ድርሻ በዝርዝር እንመለከታለን።

### ***<u>የመዋያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቁጥር 12 እና 13 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች እነርሱን በማገልገል የሚደክሙትን አገልጋዮች በተመለከተ ምን እንዲያደርጉ ይለምናቸዋል? በተጠቀሱት ሦስት ነጥቦች ላይ ተወያዩ።
2. ቁጥር 14 ን በማንብብ ለመሪዎች የተሰጡትን አራት ኀላፊነቶች በመጥቀስ በዝርዝር ተወያዩ።
3. በቁጥር 15 መሠረት በክፉ ፈንታ ክፉ ከመመለስ ይልቅ ምን ሊያደርጉ ይገባቸዋል? ክፉ ለሚያደርጉ መልካም ለማድረግ መትጋት የሚለውን ሐሳብ ተወያዩ።
4. ከቁጥር 16 እስከ 18 በማንበብ *"ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ"* የሚሉትን ሐሳቦች አንድ በአንድ ተወያዩባቸው።
5. *"ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና"* ሲል ምን ማለት እንደ ሆነ ተወያዩ።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- የእግዚአብሔር ሕዝብ በልዩ ልዩ አገልግሎት የሚደክሙትን ያውቁ ዘንድ፣ ስለ ሥራቸው በፍቅር ያከብሯቸው ዘንድ እና እርስ በርሳቸው በሰላም ይሆኑ ዘንድ ታዘዋል። አገልጋዮችም ያለ ሥርዐት የሚሄዱትን እንዲገሥጹ፣ ድፍረት የሌላቸውን እንዲያጸኑ፣ ለደካሞች እንዲተጉ እና ሰውን ሁሉ እንዲታገሱ ታዘዋል። ሌላው እያንዳንዱ አማኝ መልካምን ለማድረግ ይተጋ ዘንድ ይጠበቅበታል። ለመሆኑ ምን ያህል ድርሻንን አውቀን ኀላፊነታችንን በአግባቡ እየተወጣን ይሆን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

በልዩ ልዩ አገልግሎት የሚደክሙ አገልጋዮች እና ሕዝቡ የተሰጣቸውን ኀላፊነት በአግባቡ ከተወጡ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን በስኬት እንድትወጣ ያስችላታል። ሕዝቡ ለአገልጋዮች ሁሉ በፍቅር የሆነ አክብሮት ሊሰጥ ይገባል። እንዲሁም አገልጋዮች ሕዝቡን በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር መገሠጽና ማነጽ ይጠበቅባቸዋል። እንግዲህ እርስ በርሳችን እየተመካከርንና እየተደጋገፍን፣ አንዳችን ለሌላችን ሳናቋርጥ እየጸለይን፣ እየተቀባበልን፣ በሁሉ እያመሰገንን፣ ሁል ጊዜ በጌታ ደስ እየተሰኘን፣ በታማኝነትና በትጋት ጌታን እናገልግል። ምክንያቱም ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እኛ ነውና።

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"ማንም ለሌላው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፥ ነገር ግን ሁልጊዜ እርስ በርሳችሁ ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ።"* (1ኛ ተሰ. 5÷16)

## ***<u>ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 12</u>***

## ***<u>የመደምደሚያ ምክሮች፤ 1ኛ ተሰ. 5÷19-28</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

ባለፈው ጥናት በእግዚአብሔር ለተሾሙ አገልጋዮች እና ለሕዝቡ የተሰጡትን ኀላፊነቶች በዝርዝር ተመልክተናል። የ1ኛ ተሰሎንቄ መልእክት የመጨረሻ ክፍል በሆነው በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የሰጣቸውን ልዩ ልዩ ምክሮች በመቃኘት እናጠቃልላለን።

### ***<u>የመዋያያ ጥያቄዎች</u>***

1. ከቁጥር 19 እስከ 22 ስናነብ፣ *"መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ"* ይላል። እነዚህን ሐረጎች አንድ በአንድ በማብራራት በሚያስተላልፉት መልእክት ላይ ተወያዩ።
2. በቁጥር 23፣ *"… መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. በቁጥር 24፣ *"የሚጠራችሁ የታመነ ነው፤ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል"* የሚለው ዐረፍተ ነገር ምን ማለት እንደ ሆነና ለተሰሎንቄ ሰዎች የሚሰጠው መልእክት ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።
4. ከቁጥር 25 ጀምሮ እስከ መጨረሻው በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የሰጣቸውን ትእዛዛት በዝርዝር ተወያዩ።
5. *"ከወንድሞች ሁሉ ጋር በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- አማኞች ሁሉን በመፈተን መልካሙን ሊይዙና ከማንኛውም ዐይነት ክፉ ነገር ሊርቁ ይገባል። መመርመር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መብታችን ብቻ ሳይሆን ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ኀላፊነትም ጭምር ነው። ሌላው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ ሁለንተናችን (መንፈሳችን፣ ነፍሳችን፣ ሥጋችን) በፊቱ ያለ ነቀፋ ይሆን ዘንድ በቅድስና ልንመላለስ ይገባል።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *"መንፈስን አታጥፉ፣ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ፤ መልካሙንም ያዙ፤ ከማናቸውም ክፉ ነገር ራቁ"* በማለት ለተሰሎንቄ ሰዎች ያስተላለፈውን መልእክት የዘመኗ ቤተ ክርስቲያንም ተግባራዊ ልታደርገው ይገባል። በተለይም ከመንፈሳዊ ስጦታዎች አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ብዙ ችግሮች በሚታዩበት በዚህ ጊዜ ይህ ክፍለ ምንባብ እጅግ ጠቃሚ/ወሳኝ ነው። ሌላው ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ በፊቱ ያለ ነቀፋና ያለ ነውር እንሆን ዘንድ ሁለንተናችንን ለእርሱ እየቀደስን እንኑር! የጠራንና የሚቀድሰን ጌታ የታመነ ነው!

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።"* (1ኛ ተሰ. 5÷23)

## ሁለተኛይቱ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ስዎች

**መግቢያ**

የ1ኛ ተሰሎንቄ መልእክት ትኩረት ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ነቀፋ የሌለባቸውና ቅዱሳን ሆነው ለመገኘት እንዲተጉ ማሳሰብ መሆኑን ተወያይተናል። በዚህ በ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክት ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር በተያያዘ በአማኞች መካከል የተፈጠሩትን የተዛቡ አመለካከቶች በማረም የጌታን ዳግም ምጽአት ሲጠባበቁ ሥራ ፈቶች እንዳይሆኑ እንዴት እንደ ሞገታቸው እንመለከታለን። እንደ ተለመደው ዐውዱን በጠበቀ መልኩ የመልእክቱን ይዘት ለመወያየት ያግዘን ዘንድ የደብዳቤውን ታሪካዊ ዳራ በአጭሩ በመዳሰስ እንጀምራለን።

**ጸሐፊ**፤ የ2ኛ ተሰሎንቄ መልአክት ጸሐፊ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መሆኑ በመክፈቻ ቁጥር ላይ በግልጽ ተጽፏል፤ “ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም” (1፥1) ይላል። በተጨማሪም፣ “በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው፤ የመልእክቴ ሁሉ ማስረጃ ይህ ነው፤ እንዲህ እጽፋለሁ” (3፥17) የሚለው ሐሳብ የሐዋርያው ጳውሎስን ጸሐፊነት ያረጋግጣል። ስልዋኖስ (ሲላስ) እና ጢሞቴዎስ የሥራ ባልደረቦቹ እንደ ሆኑ ይታወቃል።

**ተቀባይ**፤ የመልአክቱ ተቀባዮች ከመጀመሪያይቱ መልእክት ተቀባዮች ጋር ተመሳሳይ እንደ ሆኑ መናገር ይቻላል፤ “በእግዚአብሔር በአባታችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን” (1፥1) የሚለው ሐሳብም ይህንኑ ሊያረጋግጥ ይችላል። የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያንን አመሠራረት በተመለከተ በ1ኛ ተሰሎንቄ መግቢያ ሥር እንደ ተጠቀሰው ከሐዋርያት ሥራ ምእራፍ 17 መረዳት ይቻላል። ይህ ምእራፍ እንደሚያመለክተው የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን አባላት አብዛኛዎቹ ከአሕዛብ ወገን ወደ ጌታ የመጡ ናቸው (የሐዋ. 17፥4 ን ከ1ኛ ተሰ. 1፥9 ጋር በማነጻጸር ይመልከቱ)። የተሰሎንቄ ከተማ በዛሬዋ ግሪክ ተብላ በምትጠራ አገር የምትገኝ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የነበራት የወደብ ከተማ መሆኗንም ማስታወስ ይቻላል።

**የተጻፈበት ጊዜና ቦታ**፤ ሐዋርያው ጳውሎስ የ1ኛ ተሰሎንቄን መልእክት ከቆሮንቶስ በ51/52 ዓ.ም አካባቢ እንደ ጻፈ መጥቀሳችን ይታወሳል። ታዲያ በተሰሎንቄ የነበረው ሁኔታ ብዙም ለውጥ ባለማሳየቱ እና በጊዜ ሊታረሙ የሚገባቸው አንዳንድ ችግሮች በመካከላቸው በመፈጠራቸው የመጀመሪያውን ደብዳቤ ከጻፈ ከስድስት ወር በኋላ (በ52ዓ.ም አካባቢ) ይህንን ሁለተኛውን መልእክት እንደ ጻፈ ይታመናል። የደብዳቤውም ይዘት ይህንኑ ያስረዳል።

**የመልእክቱ ዐላማ**፤ በዚህ አጭር መልእክት ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች እምነት በማደጉ፣ ፍቅራቸው በመጨመሩ እና በደረሰባቸው መከራ በመጽናታቸው በመደሰት እግዚአብሔርን ያመሰግናል። በተመሳሳይ መልኩ መከራው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ቢሄድም በተቀበሉት የወንጌል እውነት በመጽናት እንዲበረቱ እና ራሳቸውን ከሐሰተኞች እንዲጠብቁም ያሳስባቸዋል። ይህ ደብዳቤ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር በተያያዘ በመጀመሪያው ደብዳቤ የተላለፈውን መልእክት በአግባቡ ካለመረዳት ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ላይ ያተኩራል። በአጭሩ የ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክት አማኞች በሚገጥማቸው መከራ እንዲጸኑ ይመክራል (ምእራፍ 1)፣ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የነበራቸውን የተሳሳተ አመለካከት በማረም ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል (ምእራፍ 2)፣ እንዲሁም የጌታን ዳግም ምጽአት በመጠባበቅ ሲኖሩ ሥራ ፈቶች እንዳይሆኑ ያሳስባል (ምእራፍ 3)።

## *ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 1*

## *የምስጋናና የልመና ጸሎት፤ 2ተኛ ተሰ. 1÷1-12*

### *መግቢያ*

የ2ኛ ተሰሎንቄ የመጀመሪያ ጥናት በሆነው በዛሬው ክፍለ ምንባብ ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች በእምነታቸው እየበረቱ በመሆኑና ፍቅራቸው በመጨመሩ በመደሰት እግዚአብሔርን እንዴት እንዳመሰገነ እና አሁንም የገጠማቸውን ፈተና ሁሉ አልፈው በተቀበሉት የወንጌል እውነት ጸንተው በመጨረሻ ለክብር እንዲበቁ የጸለየላቸውን ጸሎት እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 1፣ *"… በእግዚአብሔር በአባታችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን …"* የሚለው ገለጻ ምን እንደሚያስተምር በመወያየት ጀምሩ።
2. በቁጥር 3 እና 4 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ እና ወዳጆቹ ስለ ተሰሎንቄ አማኞች እግዚአብሔርን ያመሰገኑባቸው ምክንያቶች ምን ምንድን ናቸው?
3. ከቁጥር 5 እስከ 10 በማንበብ በአማኞች ላይ መከራ በሚያመጡ ላይ እና መከራን እየተቀበሉ ባሉ ሁሉ ላይ ምን እንደሚሆን ወይም ምን እንደሚያገኛቸው ተወያዩ።
4. እነዚህ ቁጥሮች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አመጣጥ (በምን መልኩ እንደሚመጣ) እና ሲመጣ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ምን ያስተምሩናል?
5. ቁጥር 11 እና 12 ን በማንበብ ጳውሎስ እና ወዳጆቹ በተሰሎንቄ ስለ ነበሩ አማኞች የጸለዩትን የጸሎት ርእሶች በመዘርዘር ተወያዩ።

### *ከሕይወት ጋር ማዛመድ*

- በቅርብም ሆነ በሩቅ የሚያውቁን ሰዎች ሕይወታችንን ሲመለከቱ ወይም እኛን ሲያስቡ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ይመስላችኋል? ካልመሰለን በምን አቅጣጫ ራሳችንን መለወጥ እንዳለብን እናስብ። በተሰሎንቄ እንደ ነበሩ አማኞች በእምነት ማደግ፣ በፍቅር መጨመርና በመከራ መጽናት ይጠበቅብናል።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### *ማጠቃለያ*

የክርስትና ጉዞ "አልጋ በአልጋ" ሳይሆን በልዩ ልዩ መከራ የተሞላ ነው። በዚህ በወደቀ ዓለም ስንኖር የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ ዲያብሎስ ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን ተጠቅሞ ሊፈትነን ይችላል። አንዳንዴም እግዚአብሔር ክብሩን በሕይወታችን ሊገልጥ አባጣና ጎርባጦ በሆኑ መንገዶች እንድናልፍ ሊፈቅድ ይችላል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን በእምነታችን እየበረታን፣ ፍቅራችን እየጨመረ፣ በወንጌል እውነት ጸንተን መኖር ይጠበቅብናል። እንዲህ ከጸናን ጌታ ኢየሱስ ከመላእክት ጋር በክብር በሚገለጥበት ጊዜ እኛም አብረን የክብሩ ተካፋዮች እንሆናለን።

### *በቃል የሚጠና ጥቅስ*

*"ወንድሞች ሆይ እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን"* (2ኛ ተሰ. 1÷3)

***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 2***

***ማንም አያስታችሁ፤ 2ኛ ተሰ. 2÷1-12***

***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች ምንም ያህል ስደትና መከራ ቢገጥማቸውም በእምነታቸው ስለ በረቱ፣ ፍቅራቸው ስለ ጨመረና ስለ ጸኑ በመደሰት እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ እና በዚሁ ቀጥለው እስከ መጨረሻው በመጽናት ለክብር እንዲበቁ የጸለየላቸውን ጸሎት አይተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች ከጌታ ዳግም ምጽአት ጋር በተያያዘ ማንም በማንኛውም መንገድ እንዳያስታቸው እንዴት እንዳስጠነቀቃቸው እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 1 እና 2 የሚገኘውን ሐሳብ በ1ኛ ተሰሎንቄ ስለ ጌታ ምጽአት ከጻፈው ሐሳብ ጋር በማያያዝ ተወያዩ፤ በተለይም *"የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ፣ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን"* እንዲላቸው ያደረገው ምን ይመስላችኋል?
2. ከቁጥር 3 እስከ 7 በማንበብ ስለ ዐመፅ ሰው ምን እንደ ተባለ፣ ማን ሊሆን እንደሚችል እና በምን መልኩ እንደሚያስት ተወያዩ።
3. በቁጥር 6 እና 7 ላይ የዐመፅ ሰው አሁን በሙላት እንዳይገለጥ የሚከለክለው ማን/ምን ይመስላችኋል?
4. ከቁጥር 8 እስከ 10 በተጻፈው መሠረት የሐሰተኛው አመጣጥ እና የመጨረሻ ዕጣ ፈንታው ምን ይመስላል? (ራእይ 20፥10 ን በተጨማሪ ማንበብ ይቻላል)
5. ቁጥር 11-12፣ *"... ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ዛሬም መንፈሳውያን መስለው ጤናማውን አስተምህሮ እያጣመሙ የሚያስቱ እንዳሉ በመገንዘብ እንደ ቃሉ ራሳችንን ልንጠብቅ ይገባል። በወንጌላውያን አማኞች መካከል እየታዩ ያሉ የአስተምህሮ ግድፈቶችን በመጥቀስ በምን መልኩ ራሳችንን መጠበቅ እንዳለብን ተወያዩ።
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

***ማጠቃለያ***

የጌታ ዳግም ምጽአት እየቀረበ በመሆኑ የዚህ ዓለም ገዢ ጭፍሮቹን አሰማርቶ ብዙዎችን በማሳት ላይ ይገኛል። ክርስቶስ ዲያቢሎስን በመስቀል ላይ ድል በማድረጉ እኛ ክርስቲያኖች ዲያቢሎስን ልንቃወመው እንጂ ልንፈራው አይገባም። የማንኛውም ታምራት መመዘኛ የሆነውን ቃሉን ሁልጊዜ በመማር እየታጠቅን፣ በጸሎት እየተጋንና ዕለት ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እየተሞላን በንቃት ጌታን ልንጠብቀው ይገባል።

***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና።"* (2ኛ ተሰ. 2÷3)

## ***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 3***

## ***ጸንታችሁ ቁሙ፤ 2ኛ ተሰ. 2÷13-18 ፤ 3፥1-5***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ የጌታ ቀን ሲቀርብ የዐመፅ ሰው (ሐሰተኛው ክርስቶስ) ብዙዎችን ለማሳት የተለያዩ ተግባራትን እንደሚፈጽም ገልጾ የተሰሎንቄ አማኞች ማንም በማናቸውም መንገድ እንዳያስታቸው እንዲጠነቀቁ የሰጠውን ማሳሰቢያ አይተናል። በዛሬው ጥናት ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ባስተማራቸው እውነተኛ መልእክት ጸንተው እንዲቆሙ በተሰሎንቄ ለነበሩ አማኞች የሰጠውን ምክር እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 13 ላይ *"እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ቁጥር 14 እና 15 ን በማንበብ በእምነት ጸንቶ ለመቆም ቅዱሱን የእግዚአብሔር ቃል አጥብቀን መያዝ ምን ያህል እንደሚያስፈልግ ተወያዩ። ለተጨማሪ ሐሳብ 1ኛ ቆሮ. 16፥13 ተመልከቱ።
3. በቁጥር 16 እና 17 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እግዚአብሔር አባታችን ምን እንዲያደርጓቸው እንደ ተመኘ/ጸለየ ተወያዩ።
4. በምእራፍ 3 ቁጥር 1 እና 2 ላይ ሐዋርያው ስለ ምን እንዲጸልዩላቸው ጠየቀ? የጸሎት ርእሶቹን በመዘርዘር በእያንዳንዱ ላይ ተወያዩ።
5. ከቁጥር 3 እስከ 5 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያጸናቸውና ከክፉውም ሁሉ የሚጠብቃቸው ጌታ ልባቸውን ወደ ምን እንዲያቀናው እንደ ለመነ/ተመኘ ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- በማኝናውም ሁኔታ ውስጥ በጌታ ጸንተን እንድንቆም የሚያስችለን የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ለመሆኑ ቃሉን ዕለት ዕለት ምን ያህል እየተሞላን ይሆን? ሌላው ለሌሎች ቅዱሳን በተለይም ለሚያገለግሉን አገልጋዮች ምን ያህል እንጸልይላቸዋለን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

እግዚአብሔር አምላካችን የጠራን ክርስቶስን አምነን በተቀብልነው የዘላለም ሕይወት ጸንተን እርሱን እንድናከብረው እና በመጨረሻም ከእርሱ ጋር እንድንከብር ነው። በመንፈሳዊ ሕይወት እያደግን ለመሄድ እና በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ በጽናት ለመቆም ቃሉን በየዕለቱ ልንታጠቅ፣ በመንፈሱ ልንሞላና እርስ በርስ በጸሎት ልንሸካከም ይገባል። ልባችንም ጌታ ባዘጋጀልንና በሚጠብቀን የዘላለም ተስፋ ሊጸና ይገባል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ።"* (2ኛ ተሰ. 2፥15)

## ***ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጥናት 4***

## ***መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ፤ 2ኛ ተሰ. 3፥6-18***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት የተሰሎንቄ አማኞች ሐዋርያው ጳውሎስ ባስተማራቸው እውነተኛ መልእክት ጸንተው እንዲቆሙ ያቀረበላቸውን ምክር ተወያይተናል። የ2ኛ ተሰሎንቄ የመጨረሻ የጥናት ክፍል በሆነው በዛሬው ክፍለ ምንባብ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር በተያያዘ የነበረውን የተዛባ አመለካከት እንዴት እንዳረመ በተለይም ስለ ሥራ የሰጠውን ትምህርት እና የማጠቃለያ ምክሮቹን እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 6 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ እንዲለዩ የለመነበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
2. ከቁጥር 7 እስከ 9 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ *"እኛን ልትመስሉ"* በማለት እንደ ምሳሌ ያስቀመጠላቸውን ጥቀሱ፤ እንደ አገልጋይ ምሳሌ የሆነ ኑሮ በመኖር ሌሎችን መጋበዙ ምን ያስተምራል?
3. ከቁጥር 10 እስከ 13 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ ሥራ ስለማይሠሩ ሰዎች ባሕርያት የተናገረውን እና ለእነዚህ ሰዎች የሰጠውን ምክር/ትእዛዝ በጥልቀት ተወያዩ።
4. በቁጥር 13 *"እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. ከቁጥር 14-15 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ የላከውን ይህን ቃል የማይታዘዘውን ሰው ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንደሚናገር ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- የጌታን ዳግም ምጽአት በንቃት እየተጠባበቅን ስንኖር ሥራ ፈቶች ልንሆን አይገባም። ለኑሮ የሚያስፈልገንን ለማግኘት መሥራት ይጠበቅብናል። ሌላው እንደ ጳውሎስ እየሠሩ በማገልገል ለሌሎች ዓርዐያ ልንሆንም ይገባል። በዚህ ዘመን በአገልግሎት ሰበብ ሥራ መሥራት የማይፈልጉ አንዳንድ ወገኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየበዙ መምጣታቸውን እንዴት ታዩታላችሁ?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ስንጠባበቅ ያለ ሥርዐት በመሄድ፣ ለሌሎችም እንቅፋት በመሆን ሊሆን አይገባም። ልክ እንደ ጳውሎስና ወዳጆቹ በዚህም ዘመን አገልጋዮች ለሚያገለግሉት ሕዝብ በሁሉ አቅጣጫ ምሳሌ ሊሆኑ ይገባል። አማኞች ያለ ሥርዐት የሚሄዱትንና ምሳሌ የማይሆኑትን ሰዎች ሊከተሉ አይገባም። ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን ለኑሮ የሚያስፈልገንን ማግኘት እና የእግዚአብሔርን ሥራ በንጽሕና/በቅድስና መሥራት ይጠበቅብናል። እንደ አማኞች መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት!

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት፥ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፥ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም።"* (2ኛ ተሰ. 3፥8)

## የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና

**መግቢያ**

የፊልሞና መልእክት አንድ ምእራፍ ብቻ ካላቸው አራት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል አንዱ ነው (ቀሪዎቹ 2ኛ ዮሐንስ፣ 3ኛ ዮሐንስ እና የይሁዳ መልእክት ናቸው)። ይህ ደብዳቤ ሐዋርያው ጳውሎስ ከጻፋቸው ደብዳቤዎች መካከል በጣም አጭሩ ደብዳቤም ነው። ይህንን ደብዳቤ ዐውዱን በጠበቀ መልኩ ለማጥናት እና መልእክቱን በሚገባ ለመረዳት ያግዘን ዘንድ የደብዳቤውን ታሪካዊ ዳራ እንደሚከተለው በአጭሩ በመዳሰስ እንጀምራለን።

**ጸሐፊ**፤ የፊልሞና መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መሆኑና መልእክቱ ከእስር ቤት መጻፉ በደብዳቤው መግቢያ ላይ በግልጽ ተጠቅሷል፤ *"የክርስቶስ ኢየሱስ እስር ጳውሎስ ወንድሙም ጢሞቴዎስ ..."* (ቁጥር 1) ይላል። የጢሞቴዎስ ስም ከጳውሎስ ጋር መጠቀሱ አብሮ ሠራተኛ መሆኑንና በጳውሎስ ጽሑፍ ሙሉ በሙሉ የሚስማማ መሆኑን ያስታውሳል። ሌላው በቁጥር 19 ላይ *"እኔ ጳውሎስ፡- እኔ እመልሰዋለሁ ብዬ በእጄ እጽፋለሁ"* የሚለው ሐሳብ ለጳውሎስ ጸሐፊነት እንደ ተጨማሪ ማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል።

**ተቀባይ**፤ ጸሐፊው ጳውሎስ መሆኑ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ የመልእክቱ ተቀባይ ፊልሞና መሆኑ በመግቢያው ላይ ተገልጽዋል፤ *"... ለፊልሞና፣ ለእኅታችንም ለአፍቢያ፣ ከእኛም ጋር አብሮ ወታደር ለሆነ ለአርክጳ በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን"* (ቁጥር 2)። የፊልሞና ስም በመጀመሪያ ላይ መጠቀሱ የመልእክቱ የመጀመሪያው ተደራሲ እርሱ መሆኑን ያሳያል። ፊልሞና ምናልባትም በጳውሎስ አገልግሎት ወደ ጌታ የመጣ (ቁጥር 19)፣ የቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረ (ቁጥር 1-2፤ ቈላ. 4÷17) እና አናሲሞስ የሚባል ባሪያ የነበረው ሰው (ቁጥር 16) እንደ ሆነ መናገር ይቻላል።

**የተጻፈበት ጊዜና ቦታ**፤ ጳውሎስ ይህን መልእክት ከየትኛው እስር ቤት እና መቼ ጻፈ በሚለው ዙርያ በምሁራን ዘንድ የሐሳብ ልዩነት ቢኖርም በትውፊት ከሮም እስር ቤት ከ61-63 ዓ.ም ባለው ጊዜ እንደ ተጻፈ ይታመናል። ይህም በሮም የነበረውን የመጀመሪያውን እስራቱን ያሳያል (የሐዋ. 28÷15-31)። ሌላው ወደ ፊልሞና በተጻፈው መልእክት (ቁጥር 1-2) እና በቈላስይስ 4÷9-10፤ 2÷14) የተጠቀሱት ሰዎች ተመሳሳይ መሆናቸው ፊልሞና ይኖር የነበረው በቈላስይስ እንደ ሆነ እንዲሁም ሁለቱም መልእክቶች የተጻፉትና የተላኩት በተመሳሳይ ጊዜ እንደ ነበር ያመለክታሉ። ሌላው አናሲሞስ የመልእክቱ አድራሽ እንደ ሆነ ከሚታሰበው ከቲኪቆስ ጋር ወደ ፊልሞና እንደ ተላከ ይታመናል (ከቈላስይስ 4÷7-9 ጋር በማነጻጸር ያንብቡ)።

**የመልእክቱ ዐላማ**፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መልእክት ለፊልሞና የጻፈበት ዋና ምክንያት ከእርሱ አምልጦ የሄደውን ባሪያውን አናሲሞስን በሚመለከት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ነው። በሮማውያን ሕግ መሠረት አምልጦ የሄደ ባሪያ የሚቀጣው በሞት ነው። ጳውሎስ የአናሲሞስ አማላጅ በመሆን ፊልሞናን አጥብቆ የሚለምነው አናሲሞስን ወደ እርሱ በሚመለስበት ጊዜ እንደ ክርስቲያን ወንድም በመቁጠር እርሱን (ጳውሎስን) በሚቀበልበት ፍቅር እንዲቀበለውና በመልካም ዐይን እንዲያየው ነው።

## ***<u>ወደ ፊልሞና ጥናት 1</u>***

## ***<u>ሰላምታ፣ ምስጋና እና ጸሎት፤ ፊልሞና 1-7</u>***

### ***<u>መግቢያ</u>***

በፊልሞና መልእክት ላይ በምናደርገው በዚህ በመጀመሪያው ጥናታችን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ መግቢያ የሰጠውን ሰላምታ እና ስለ ፊልሞና እምነትና ፍቅር እንዲሁም የቅዱሳንን ልብ በማሳረፉ በመደሰት እግዚአብሔርን እንዴት እንዳመሰገን እንመለከታለን።

### ***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. የደብዳቤው ጸሐፊ የሆነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቁጥር 1 ላይ ራሱን ያስተዋወቀው እንዴት ነው? *"የክርስቶስ ኢየሱስ እስር"* ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ሐዋርያው ጳውሎስ የደብዳቤው ተቀባይ የሆነውን ፊልሞናን የገለጸው ምን በማለት ነው? ይህ ገለጻ በሁለቱ መካከል ስላለው ግንኙነት ምን እንደሚጠቁመን ተወያዩ።
3. በቁጥር 4 እና 5 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ፊልሞና የሰማውና እግዚአብሔርን የምያመሰግንባቸው ምክንያቶች ምን እና ምንድን ናቸው?
4. በቁጥር 6 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልሞና የሚጸልየው ስለ ምንድን ነው?
5. በቁጥር 7፣ *"የቅዱሳን ልብ በአንተ ሥራ ስለ ዐረፈ ወንድሜ ሆይ በፍቅርህ ብዙ ደስታንና መጽናናትን አግኝቼአለሁና"* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።

### ***<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>***

- ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ፊልሞና ከሌሎች ሰዎች ስለ ሰማው መልካም ምስክርነት በመደሰት እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ፊልሞና በጌታ በኢየሱስ ያለው እምነት እና ለቅዱሳን ሁሉ ያሳየው ፍቅር በሌሎች ዘንድ የተገለጠ ነበር። ዛሬስ እኛ በሌሎች ዘንድ ያለን ምስክርነት ምን ይመስላል? ለመሆኑ በሌሎች ዘንድ የምንታወቀው ወይም እኛ በሌለንበት ሰዎች ስለ እኛ የሚናገሩት ምን ይሆን?
- በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተካተቱ ነጥቦችን በመጥቀስ ተወያዩ።

### ***<u>ማጠቃለያ</u>***

ሐዋርያው ጳውሎስ በእስር ላይም ሆኖ ሳለ ስለ ሌሎች ግድ በመሰኘት ይህን ግላዊ መልእክት መጻፉ ለአገልግሎት ያለውን ልብ ያሳያል። በመልእክቱ መግቢያ ላይ ፊልሞናን ያስተዋወቀበት መንገድ እና ስለ ፊልሞና ከሌሎች በሰማው መልካም ምስክርነት በመደሰት እግዚአብሔርን ማመስገኑ አስተማሪ ነው። ሌላው ስለ ፊልሞና እምነትና ለሌሎች ስለ ነበረው ፍቅር ከቀረበው መልካም ምስክርነት በመነሳት ራሳችንን ልንመረምር ይገባል። ዛሬ ላይ ሌሎች ስለ እኛ መልካም ምስክርነት ይሰጣሉ?

### ***<u>በቃል የሚጠና ጥቅስ</u>***

*"በጌታ በኢየሱስ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ ዘንድ ስላለህ ስለ ፍቅርህና ስለ እምነትህ ሰምቼ በጸሎቴ እያሳሰብሁ ሁልጊዜ አምላኬን አመሰግናለሁ።"* (ፊልሞና 4-5)

***ወደ ፊልሞና ጥናት 2***

**ጳውሎስ ስለ አናሲሞስ ለፊልሞና ያቀረበው ጥያቄ (ክፍል አንድ)፤ ፊልሞና 8-16**

***መግቢያ***

በጥናት አንድ ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱንና የደብዳቤው ተቀባይ የሆነውን ፊልሞናን ያስተዋወቀበትን መንገድ እንዲሁም ስለ ፊልሞና ከሌሎች በሰማው ምስክርነት በመደሰት እግዚአብሔርን እንዴት እንዳመሰገነ ተነጋግረናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጳውሎስ ስለ አናሲሞስ ለፊልሞና ያቀረበውን ጥያቄ እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 8-9 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ፊልሞናን ማዘዝ እየቻለ *"ስለ ፍቅር እለምንሃለሁ"* በማለት ጥያቄውን በፍቅር ማቅረቡ ምን ያስተምረናል?
2. ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልሞና በፍቅር ያቀረበው ጥያቄ ምንድን ነው? (ቁጥር 10-11)፤ በማያያዝ *"አንተም ልቤ እንደሚሆን ተቀበለው"* (ቁጥር 13) ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ።
3. *"በእስራቴ ስለ ወለድሁት ስለ ልጄ ስለ አናሲሞስ ..."* ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ሐዋርያው ጳውሎስ በእስራቱ የወለደውን አናሲሞስን ለራሱ ሊያስቀረው ፈልጎ ያላደረገው ለምንድን ነው? (ቁጥር 14)
5. ፊልሞና አስቀድሞ ባሪያው የነበረውን አናሲሞስን ከእንግዲህ በኋላ በምን መልኩ ሊይዘው ይገባል? ለመሆኑ በአናሲሞስ ሕይወት ይህ ለውጥ እንዲመጣ ያደረገው ምንድን ነው? (ቁጥር 15-16)

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- በአናሲሞስ ሕይወት የመጣው ለውጥ እና ፊልሞና እንደ ወንድም እንዲቀበለው የቀረበለት ጥያቄ ወንጌል ምን ያህል የማይጠቅምን ሰው ጠቃሚ እንደሚያደርግ እና በማኅበረ ሰብ ውስጥ ያለን የተበላሸ ሥርዐት/መዋቅር እንደሚያስተካከል ሊያሳይ ይችላል። ሌላው ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልሞና ጥያቄውን ያቀረበበት መንገድ በመመልከት ግንኙነቶቻችንን ልንፈትሽ ይገባል።
- በዛሬው የጥናት ክፍል የመወያያ ጥያቄዎች ያልተካተቱ ሐሳቦች ካሉ በመጥቀስ ተወያዩ።

***ማጠቃለያ***

በልዩ ልዩ ምክንያት ሁለት የተቀያየሙ ሰዎችን መልሰው እንዲቀባበሉ ለማድረግ የሐዋርያው ጳውሎስ ዐይነት ልብ ይፈልጋል። ይህም ልብ የክርስቶስ ዐይነት ልብ ሲሆን በይቅር ባይነት የሚታወቅ፣ በቃሉ የሚመራ፣ በጸሎት የሚተጋ፣ ሰውን የሚያከብር፣ በፍቅርና በርኅራኄ የተሞላ፣ ስለ ሌሎች ሰዎች የሚገደው አዛኝ ልብ ነው። ይህ ከእኛም ይጠበቃል፤ የይቅርታ ልብ ሊኖረን ይገባል። ሌላው የፊልሞና ለውጥ ወንጌል በግለ ሰብ ሕይወትና በማኅበረ ሰብ መካከል የሚያመጣውን ለውጥ ሊያሳይ ይችላል።

***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"ከእንግዲህ ወዲህ እንደ ባሪያ አይሆንም ነገር ግን ለእኔ በተለየ የተወደደ ወንድም ከሆነ ለአንተማ ይልቅ በሥጋውም በጌታም ዘንድ ከባሪያ የሚሻል የተወደደ ወንድም እንዴት አይሆንም።"* (ፊልሞና 16)

## ***ወደ ፊልሞና ጥናት 3***

## ***ጳውሎስና ስለ አናሲሞስ ለፊልሞና ያቀረበው ጥያቄ (ክፍል ሁለት)፤ ፊልሞና 17-25***

### ***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልሞና በፍቅር ያቀረበውን ጥያቄ ማለትም አናሲሞስን እንደ ባሪያ ሳይሆን እንደ ወንድም እንዲቀበለው መለመኑን ተወያይተናል። በዛሬው ጥናታችንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እርሱን በሚቀበልበት መንገድ አናሲሞስን እንዲቀበል፣ በአንዳች ነገር የበደለ ቢሆን ወይም ብድር ያለበት ቢሆን በእርሱ ላይ እንዲቆጥር ለፊልሞና ያቀረበውን ጥያቄ እና የደብዳቤውን መዝጊያ እንመለከታለን።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. የዛሬው ክፍለ ምንባብ በሐዋርያው ጳውሎስ እና በፊልሞና መካከል ስላለ ግንኙነት ምን ይጠቁመናል? (ቁጥር 17፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22)
2. ሐዋርያው ጳውሎስ ከፊልሞና ጋር ያለውን ግንኙት መሠረት በማድረግ *"እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው"* ማለቱ እና *"... ብድር ያለበት እንደ ሆነ ይህን በእኔ ላይ ቁጠር እኔ ጳውሎስ እኔ እመልሰዋለሁ ..."* ማለቱ ምን ዐይነት ትምህርት እንደሚሰጥ ተወያዩ።
3. በቁጥር 18 ላይ የሚገኘውን ሐሳብ ከቁጥር 10-11 እና ከቁጥር 16 ጋር በማገናኘት በፊልሞና እና በአናሲሞስ መካከል የተፈጠረው ችግር ምን ሊሆን እንደሚችል ተወያዩ።
4. በቁጥር 21 ሐዋርያው ጳውሎስ *"ከምልህ ይልቅ አብልጠህ እንድታደርግ አውቄ እንድትታዘዝም ታምኜ እጽፍልሃለሁ"* ማለቱ ለፊልሞና ምን ዐይነት መልእክት የሚያስተላልፍ ይመስላችኋል?
5. ከቁጥር 23 እስከ 25 በማንበብ ይህ አጭር ደብዳቤ የተቋጨበትን መንገድ እና በመዝጊያ ሐሳቡ ውስጥ ያሉትን ቁም ነገሮች ተወያዩ።

### ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

- ➢ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ባሪያ የነበረውን እና አንዳች ዐይነት ጥፋት ያጠፋውን አናሲሞስን ከፊልሞና ጋር ለማስታረቅ የሄደበት ርቀት ያስደንቃል። ሐዋርያው ጳውሎስ ወዳጁ ፊልሞና ባሪያው የነበረውን አናሲሞስን እርሱን በሚቀበልበት መንገድ እንዲቀበለው እና ብድርም ካለበት በእርሱ ላይ እንዲቆጥር መጠየቁ ሞጋች ነው። ለመሆኑ እኛስ የተጣሉትን ለማስታረቅና የበደሉንን ይቅር ለማለት ዝግጁ ነን?
- ➢ በዛሬው ክፍለ ምንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተዳሰሰ ሐሳብ ካለ ተወያዩበት።

### ***ማጠቃለያ***

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልሞና እና በአናሲሞስ መካከል የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት የሄደበት ርቀት አስተማሪ ነው። በተለይም የአናሲሞስ የትኛውም ጥፋት/ችግር በእርሱ ላይ እንዲቆጠር እና ዋጋ ሊከፍልለት ፈቃደኛ መሆኑን መግለጹ ሞጋች ነው። እኛም በተለያዩ መንገዶች ጎድተውን የሄዱትን ሰዎች ስለ ክርስቶስ ይቅር በማለት መልሰን ለመቀበል ዝግጁዎች ልንሆን ይገባል። እግዚአብሔር ለሌሎች የሚገደው፣ በፍቅርና በርኅራኄ የተሞላ፣ ይቅር ባይ ልብ እና ስለ ለሌሎች ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ የሆነ ማንነት ከእኛ ይፈልጋል።

### ***በቃል የሚጠና ጥቅስ***

*"እንግዲህ እንደ ባልንጀራ ብትቆጥረኝ እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው። በአንዳች ነገር የበደለህ ቢኖር ግን ወይም ብድር ያለበት እንደ ሆነ ይህን በእኔ ላይ ቁጠር"* (ፊልሞና 17-18)